# የባህር ኃይል እና የኢትዮጲያ ብሔራዊ ደኅንነት ቅንጦት ወይስ የሕልውና ጉዳይ

**ካፒቴን ከበደ ሚካኤል መንገሻ[1] እና አዲስ ዓለማሁ ገብረማሪያም[2]**


## *አጽርኦት*

*በዓለማችን በርካታ ሃገራት የባህር ኃይል የሚያቋቁሙት የባህር ክልላቸውን ለማስጠበቅ ሲሆን ከዚህም ባሻገር ሃገራቱ አለማቀፉን የባህር ደህንነት ለመጠበቅ፤ የባህር ላይ ውንብድናን በመከላከል በምድር አካል ላይ በመሆን ሊመከቱ የማይችሉ የጠላት ኃይል እንቅስቃሴን ለመመከት፤ በዓለም-አቀፉ የባህር ክልል ላይ ለሚደረጉ የተፈጥሮ ሃብት ጥበቃና ልማት ላይ ለመሰማራት፤ የባህር ላይ ህገ ወጥ የሰው ዝውውርና የመሳሪያ ሽያጭን ለመቆጣጠር የባህር ሃይላቸውን የሚያጠናክሩበት ሁኔታ አለ። አሁን አሁን የባህር በር የሌላቸው በርካታ የዓለማችን ሃገራት ሳይቀሩ የባህር ኃይል ያቋቋሙበት ሁኔታ መኖሩን መረዳት ይቻላል። በዓለማችን ላይ የባህር በር ያላቸውም የሌላቸው ሃገራት በተመሳሳይ የንግድ መርከቦቻቸውን ደህንነት መጠበቅ፤ ለሁሉም ክፍት የሆነውን ዓለም-አቀፍ የባህር እና የውቅያኖስ አካልን መጠቀም፤ ሽብርተኝነትና እና የባህር ላይ ውንብድናን መከላከል ይጠበቅባቸዋል። ኢትዮጲያ ከታላላቅ የአለማችን የውሃ አካል (ቀይ ባህር እና ህንድ ውቅያኖስ) ያልራቀችና በቅርብ ርቀት የምትገኝ ሃገር ነች። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የአለማችን ሃያላን ሃገራትን ጨምሮ በርካታ የባህረ ሰላጤው ሃገራት በአፍሪካ ቀንድ (በቀይ ባህርና በህንድ ውቅያኖስ ዳርቻዎች) የወደብ ግንባታ እና የወታደራዊ ጦር ሰፈር ምስረታ ፉክክር ውስጥ መግባታቸው ይታወቃል። ሃገራችን ኢትዮጲያ በቀጠናው ያለው የሃገራቱ የጦር ሰፈር ምስረታና የወደብ ግንባታ እሽቅድድም ነገሮችን በጥሞና በመመልከት ለንግድ መርከቦቿ ደህንነት እና በአካባቢው ያለው ፉክክር ወደ ፊት ሊያመጣ የሚችለውን አሉታዊ ተፅዕኖ ግምት ውስጥ በማስገባት የኢትዮጲያን ብሄራዊ ጥቅም እና የንግድ መርከቦቿን ደህንነት አስተማማኝ በሆነ መንገድ ለማስጠበቅ በአዋጅ ቁጥር 1100/2011 መሰረት የኢትዮጲያ ባህር ኃይል የመከላከያ ሃይሎች አካል ሆኖ ተቋቁሞ ወደ ስራ ገብቷል። ይህ ጥናትም በዋነኛነት በኢትዮጲያ የባህር ኃይል መቋቋሙ እንድምታውን የሚዳስስ ሲሆን በኢትዮጲያ የባህር ኃይል መቋቋም ላይ ያሉ አዎንታዊ እና አሉታዊ አመለካከቶች ላይ ጥልቅ ዳሰሳ በማድረግ ባህር ኃይል ለኢትዮጲያ ቅንጦት ወይስ የህልውና ጉዳይ የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ነው። የጥናቱ መነሻ ችግርም በኢትዮጲያ የባህር ኃይል እንዲቋቋም መደረጉ የተለያዩ አካላት፣ ሚዲያዎች እና ዜጎች የተለያየ አዎንታዊ፣ አሉታዊ እና የተዛቡ ምልከታቸውን እያንጸባረቁ ይገኛሉ። ይህን እንደ ጥናት የባህር ኃይልን አስፈላጊነት የሚዳስስ፣ በቀጠናው ያሉ የሃያላን ሽኩቻና በባህር ኃይል መመስረት ዙሪያ የሚታዩ የተዛቡ አመለካከቶች እንዴት መቅረፍ እንደሚቻልም በጥልቀት በማጥናት የኢትዮጲያን የውሃ ላይ ደህንነት እና ብሄራዊ ጥቅም ማስጠበቅ የሚችል ተወዳዳሪ የሆነ ባህር ኃይል ለመገንባት ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ምክረ-ሃሳቦችን ለማቅረብ ያለመ ነው።*


**ቁልፍ ቃላት:** ኢትዮጲያ፣ ባህር ኃይል፣ ቀይ ባህር፣ ብሔራዊ ደኅንነት፣ የባህር በር፣ የአፍሪካ ቀንድ

## 1. መግቢያ

የባህር ኃይል በዓለማችን በዘመናዊ እሳቤ መታሰብ የጀመረው በ11ኛው ክፍለ ዘመን ነው። ነገር ግን ጥንታዊ ስልጣኔ በነበረባቸው እንደ ግሪክ፣ ሮም፣ ህንድ እና ፐርሺያ መንግስታት ባህር/ውቅያኖስ አቋራጭ መርከቦችን ወይም ትላልቅ ጀልባዎችን መጠቀም ከጀመሩበት ግዜ አንስቶ የንግድ መርከቦቻቸውን/ጀልባዎቻቸውን የሚያስጠብቁበት ከንግድ መርከቦች ጋር አብሮ የሚሰማራ የጥበቃ ቡድን ያሰማሩ እንደ ነበረ ታሪክ ይነግረናል።

በመካከለኛው ክፍለ ዘመን ከስፔን እና ፖርቹጋል የዓለም አሰሳ ጋር በተያያዘ የባህር ኃይል አስፈላጊነቱ እየጎላ የታየበት ጊዜ ነበር። በመቀጠልም እንግሊዝና ፈረንሳይ ሃሳቡን በደንብ እያዘመኑ የባህር ኃይል እያደራጁ መጡ። በእንግሊዝ የሮያል ባህር ኃይል በአስራ ስድስተኛ ክፍለ ዘመን በሄነሪ ስምንተኛ እንደተቋቋመና ስመጥር የባህር ኃይል እንደሆነ ይነገራል።[3] ከዚሁ ግዜ አንስቶ መድፎችንና ከባድ መሳሪያዎችን የሚታጠቁ የባህር ሃይሎች በዓለማችን ላይ ብቅ ብቅ ማለት ጀመሩ። ከሁለተኛው

[1] የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ባህር ኃይል ምክትል አዛዥ ለትምህርትና ሥልጠና (ተወካይ)፤ kebmicmen@gmail.com

[2] በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ውጭ ጉዳይ ኢኒስቲትውት የመካከለኛው ምስራቅ ጉዳዮች ተመራማሪ፤addisalemahu@yahoo.com

[3] Davies, C. S. L. “The Administration of the Royal Navy under Henry VIII: The Origins of the Navy Board.” The English Historical Review 80, no. 315, 1965: 268–88.

የዓለም ጦርነት ወዲህ በዓለም ላይ የባህር ኃይል በአይነትም፣ በዘመናዊነትም እንዲሁም በብዛት እየተሻሻለ እና እየዘመነ ዛሬ የደረሰበት ደረጃ ለመድረስ ችሏል።

በኢትዮጲያ  የባህር ኃይል ታሪክ ኤርትራ በፌዴሬሽን ከኢትዮጲያ ጋር መቀላቀሏን ተከትሎ እንደ እ.ኤ.አ. በ1955 የተመሰረተ ሲሆን መቀመጫውን ምጽዋ አድርጎ በአሰብ፣ በአስመራ እና በዳህላክ ደሴቶች ማዘዣዎች ነበሩት። የኢትዮጲያ የባህር ኃይል የንጉሳዊው አገዛዝ ካበቃም በኋላ የቀጠለ ሲሆን ባህር ሃይሉ የቆመው የኤርትራ ሃገረ መንግስት መቋቋሙን ተከትሎ ሃገሪቱ የባህር በር በማጣቷ ነው። ከዓለም ታሪክ ለመረዳት እንደሞከርነው መንግስታት ባህር እና ውቅያኖስ አቋራጭ የንግድ መርከቦቻቸውን ደህንነት ለመጠበቅ ለእጀባ እና ለደህንነት ይጠቀሙ እንደነበረ እና አሁን ደግሞ የባህር ኃይል ዘርፈ ብዙ በሆኑ ከብሄራዊ ህልውና ጋር በሚያያዙ ምክንያቶች እንደሚያስፈልግ ግልጽ እየሆነ የመጣ ጉዳይ ነው።

ብዙ ሃገራት የባህር ኃይል የሚያቋቁሙት የባህር ክልላቸውን ለማስጠበቅ ሲሆን ከዚህም ሲያልፍ ዓለም-አቀፉን የባህር ደህንነት ለመጠበቅ፤ ለትላልቅ የጦር መሳሪያ ሽያጭ ማጓጓዣነት፤ የባህር ላይ ውንብድናን በመከላከል የንግድ መርከቦቻቸውን ደህንነት ለማስጠበቅ፤ በምድር አካል ላይ በመሆን ሊመከቱ የማይችሉ የጠላት እንቅስቃሴን ለመመከት፤ በዓለም-አቀፉ የባህር ክልል ላይ ለሚደረጉ የተፈጥሮ ሃብት ጥበቃና ልማት ላይ ለመሰማራት፤ የባህር ላይ ህገ-ወጥ የሰው ዝውውርና የመሳሪያ ሽያጭን ለመቆጣጠር ታሳቢ እያደረጉ ነው። ከሁሉም በላይ በዓለም-አቀፉ መርህ መሰረት ማንኛዉም ሃገር ከዓለም-አቀፉ ባህርን የመጠቀም መብት እንዳለው ድንጋጌዎች ተቀምጠዋል[4]። ከባህርና ከውቅያኖስ ባሻገር ደግሞ በሁለት ወይም በሶስት ሃገራት መካከል በአህጉር ውስጥ ያለ የባህር ወይም የውሃማ አካላት የወሰን ጥበቃ እና ፍትሃዊ  የሆነ የውሃ ሃብት አጠቃቀም መብትን ለመጠበቅም የባህር ኃይል አስፈላጊ ነው።

ኢትዮጲያ የባህር ክልል ባይኖራትም ከላይ ከተጠቀሱት ከአንዱ ግዳጅ በስተቀር (የባህር በር ወይም የባህር ወሰን ክልል ለማስጠበቅ) ከሚለው ባሻገር ሁሉም ልትከውናቸው የሚገቡ መብቶች፣ ግዴታዎችና የሚጠበቁ ድርሻዎች ናቸው። የባህር በር የሌላቸው በአፍሪካ በአውሮፓ እና በላቲን አሜሪካ የሚገኙ በርካታ የአለማችን ሃገራት ሳይቀሩ የባህር ኃይል ያቋቋሙበት ሁኔታ መኖሩን መረዳት ይቻላል። አንዳንዶቹ በተናጥል ራሱን የቻለ የባህር ኃይል ሲያቋቁሙ አንዳንዶቹ የባህር በር ካላቸው አጋሮቻቸው ወይም የጎረቤት ሃገራት ጋር በጣምራ ያቋቋሙበት ሁኔታ አለ። ለምሳሌ አዝርባጃን፣ ካዛኪስታን፣ ላኦስ፣ ቱርክሚስታን፣ ፓራጓይ፣ ሩዋንዳ፣ ማእከላዊ አፍሪካን ሪፐብሊክ፣ ቦሊቪያ እና ኡጋንዳን መጥቀስ ይቻላል።

የባህር በር የሌላቸው ሃገራት የንግድ መርከቦቻቸውን ደህንነት ለመጠበቅ፤ ለሁሉም ክፍት የሆነውን ዓለም-አቀፍ የባህር እና የውቅያኖስ አካል ለመጠቀም፤ ሽብርተኝነትና እና የባህር ላይ ውንብድናን በመከላከል ሂደት ውስጥ መሳተፍ አለባቸው። በተጨማሪም ሃገራት ድንበር ተሻጋሪ የሆኑ ታላላቅ ሃይቆች እና ወንዞች በፍትሃዊነት ለመጠቀምና ደህንነቱን ለመጠበቅ ይረዳ ዘንድ የባህር ኃይል ወደ ማቋቋም የገቡበት ሁኔታ አለ። ለምሳሌ ያክል ሩዋንዳ ከዲሞክራቲክ ኮንጎ ጋር በሚያዋስናት በኪቩ ሃይቅ፤ ኡጋንዳ ደግሞ በቪክቶሪያ ሃይቅ አማካኝነት ከኬንያ እና ታንዛኒያ የምትዋሰን ሲሆን፤ ከላቲን አሜሪካም ፓራጉዋይ በፓራጉዋይ  ወንዝ ከአርጀንቲና ጋር ድንበር ስለምትጋራ የራሳቸው የሆነ የባህር ኃይል አላቸው። በአውሮፓም በተመሳሳይ የባህር በር የሌላቸው በርካታ የባልካን ሃገራት ተመሳሳይ የባህር ኃይል ያቋቋሙበት ሁኔታ አለ።

ኢትዮጲያ ከታላላቅ የአለማችን የውሃ አካል (ቀይ ባህር እና ህንድ ውቅያኖስ) ያልራቀችና በቅርብ ርቀት የምትገኝ ሃገር ነች። አገራችን ኢትዮጲያ ከቀይ ባህር በ60 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ከህንድ ውቅያኖስ ደግሞ 300 ኪሎ ሜትር በማይሞላ ርቀት ላይ ትገኛለች። በተጨማሪም በምስራቅ አፍሪካ ትልቁን ጥቅል ምርት ወደ ውጪ የምትልክ ሃገር እንደመሆኗ 90 ፐርሰንት የሚሆነውን ምርቶች ወደ ውጪ የምታስወጣው እና የምታስገባው በዚህ መስመር መሆኑ ነገሮችን ቆም ብላ ማሰብ እንዳለባት ያመላክታል።

ከሁለት አስርት አመታት ወዲህ የአለማችን ሃያላን ሃገራትን ጨምሮ በርካታ የባህረ ሰላጤው ሃገራት በአፍሪካ ቀንድ እና በአካባቢው የወደብ ግንባታና እና የወታደራዊ ሰፈር ማቋቋም ፉክክር ውስጥ መግባታቸው[5] ኢትዮጲያ ነገሮችን በጥሞና እንድትመለከትና ይዞት ሊመጣ የሚችለውን ጫና በመረዳት ለንግድ መርከቦቿ ደህንነት እና በአካባቢው ያለው ፉክክር ወደ ፊት ሊያመጣ የሚችለውን ስጋት ግምት ውስጥ በማስገባት ባህር ኃይል ለማቋቋም ወስና ወደ ስራ ገብታለች። በተጨማሪም የሶማሊያ እና የህንድ ውቅያኖስ የአፍሪካ ዳርቻዎች ከአለማችን ግንባር ቀደም የባህር ላይ ውንብድና ይታይባቸዋል ከሚባሉት

[4] "United Nations Convention on the Law of the Sea." United Nations. https://www.un.org/depts/los/convention_agreements/texts/unclos/part2.htm , Accessed on 3 January 2023.

[5] Horton, M. Hot Issue - The Race for Bases, Ports, and Resources in the Horn of Africa Heats Up – Jamestown Foundatin. 11 October 2019. https://jamestown.org/program/hot-issue-the-race-for-bases-ports-and-resources-in-the-horn-of-africa-heats-up/, Accessed on 3 January 2023

አካባቢዎች ዋናው ነው። ይህ ደግሞ ለኢትዮጲያ ከህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር፣ ህገ-ወጥ ንግድ፣ ህገ-ወጥ የመሳሪያ ዝውውር እና ከሽብርተኝነት ጋር ለተያያዙ ስጋቶች እንደ ዋነኛ የስጋት ምንጭ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል።

ኤርትራ በፌዴሬሽን ከኢትዮጲያ ጋር መዋሃዷን ተከትሎ እ.ኤ.አ. በ1955 የባህር ኃይል እንዳቋቋመች ይታወቃል። ከኤርትራ ሃገረ መንግስት ምስረታ በፊት ኢትዮጲያ በቀይ ባህር በኩል 1000 ኪሎ ሜትር የባህር በር ነበራት። በወቅቱ በዩናይትድ ኪንግደም የሚታገዝ ዋና ማዘዣ ጣቢያውን ምፅዋ ያደረገ የባህር ኃይል እንደነበራት ይታወቃል። ከንጉሳዊው ዘመን ባሻገርም ይህ የባህር ኃይል በወታደራዊው መንግስት የቀጠለ ሲሆን በዚህ ወቅትም በተወሰነ መልኩ በቀድሞዋ ሶቭየት ህብረት መንግስት የቴክኒካል ድጋፍ ይደረግለት ነበር። የባህር ኃይል በኢትዮ-ሶማሌ ጦርነት ወቅት አበርክቶ ባለማድረጉ ምክንያት በደርግ ዘመነ መንግስት ትልቅ ትኩረት እንዳልተሰጠው አንዳንድ መጻህፍት ይገልጻሉ።

የኢትዮጲያ ባህር ኃይል ከሬፍረንደም በኋላ እ.ኤ.አ በ1993 የኤርትራ ሃገረ መንግስት መመስረትን ተከትሎ ኢትዮጲያ የነበራት የባህር በር በማጣቷ እንዲፈርስ ሆኗል። ላለፉት 30 አመታትም ሃገሪቱ የባህር ኃይል ሳይኖራት ቀርቷል።

ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተበራከቱ በመጡ የዓለም አቀፊ ተለዋዋጭ አስገዳጅ መንስኤዎች ኢትዮጲያ የባህር ኃይል ሊኖራት ግድ አስብሏል። ለምሳሌ የአፍሪካ ቀንድ በሃያላን ሃገራት እና በባህረ ሰላጤው ሃገራት እይታ ውስጥ በመግባቱ አካባቢው ላይ ለመስፈር እና ተፅዕኖ ለመፍጠር ከፍተኛ ፉክክር እየታየ ነው። ፉክክሩም እጅግ ቀጣይነት ባለው ሁኔታ እየተስፋፋ ይገኛል።[6] ለምሳሌ በጅቡቲ የፈረንሳይ፤ ቻይና እና አሜሪካ የጦር ሰፈር መኖሩ፤ በሶማሌ ላንድ የተለያዩ የባህረ ሰላጤው ሃገራትና ቱርክ በአካባቢው የወደብ ግንባታ ፍላጎት ማሳየታቸው፤ በተጨማሪም እነዚሁ ሃገራት የጦር ሰፈር ማቋቋማቸው ቀጠናው ምን ያህል ሳቢ መሆኑን ያሳያል።[7] ኢትዮጲያ ወደ ውጭ ከምትልከው ዋቅል ምርቷ 90 ከመቶ የሚሆነው በዚሁ መስመር የሚተላለፍ እንደመሆኑ ሃገሪቱን ስጋት ላይ ከቶ ይገኛል። በተጨማሪም ከቅርብ ግዜ ወዲህ የቀይ ባህር ተዋሳኝ ሃገራት የመሰረቱት *"የቀይ ባህር ፎረም"* ህብረት ኢትዮጲያ በስልሳ ማይል ርቀት ላይ ሆና ሳለ ጥምረቱ ኢትዮጲያን ማግለሉ እና ከየመን ቀውስ ጋር በተያያዘ የባቢል ኤል መንደብ የባህር ሰርጥ እና የባህረ ገብ ቦታዎች የስጋት ቀጠና እየሆነ መምጣቱ ኢትዮጲያን እያሳሰበ ይገኛል።[8] የኢትዮጲያ መንግስትም እነዚህ እንቅስቃሴዎች በቀጣይ ሊያመጡ የሚችሉትን ተፅዕኖዎች በማሰብ የሀገሪቱን እና የንግድ መርከቦቿን ደህንነት አስተማማኝ በሆነ መንገድ ለማስጠበቅ የባህር ኃይል አቋቁሟል። ይህም መሆኑ እንዴት የራሷ ባህር የሌላት ሀገር የባህር ኃይል ታቋቁማለች የሚል ጥያቄ አጭሯል።

## 2. የባህር ኃይል አመሰራረት ታሪክ በኢትዮጲያ

በ1947 ዓ.ም. የኢትዮጲያ ሮያል የባህር ኃይል "የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የባህር ኃይል" የሚል ኦፊሴላዊ ስም ተሰጥቶት ቋሚ የጦር ሠፈሩን በምፅዋ ወደብ ላይ አቋቋመ። በ1950 ዓ.ም. ላይ ሦስት ተከታታይ ዓመታትን የፈጀው ታላቅ የግንባታ ሥራው ሲጠናቀቅ የኢትዮጲያ ሮያል የባህር ኃይል ከንጉሠ ነገሥቱ የምድር ጦር እና ከንጉሠ ነገሥቱ የአየር ኃይል በመቀጠል በኢትዮጲያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት የጦር ኃይሎች ጠቅላይ መምሪያ ሥር በሦስተኛነት ተደመረ።

የኢትዮጲያ ሮያል የባህር ኃይል ታሪክ እንደሚያስረዳው ሲቋቋም ጀምሮ ዋና ግዳጁ የነበረው በቀይ ባህር ጠረፎች ላይ ቁጥጥርና አሰሣ የማድረግ ቋሚ የቅኝት ግዳጅ ሲሆን ዋና ማዘዣውን አዲስ አበባ እና ምፅዋ ላይ በማድረግ፣ በመጀመሪያ በክብር ዘበኛና የምድር ጦር ምክትል ዋና አዛዥ ሥር፣ በመቀጠልም የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ በሆኑት በንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘ-ኢትዮጲያ ዋና የጦር አዛዥነት ሥር እንዲመራ ተደረገ። የኢትዮጲያ ሮያል የባህር ኃይል በቆይታው ዘመን የናቫል ኦፊሰሮች ማሰልጠኛ ኮሌጅ በአስመራ፣ የዳይቪንግ ማሰልጠኛ ኮሌጅ በምፅዋ፣ የስፔሻል ኮማንዶ ዩኒት ማሠልጠኛ ኮሌጅ በምፅዋ፣ በአሰብና በአስመራ፣ እና የባህር ኃይል የመገናኛና ዋገና ኮሌጅ በቀይ ባህር ዳህላክ ደሴት ላይ እንዲቋቋሙ ከማድረጉም በላይ በንጉሠ ነገሥቱ መልካም ፈቃድና ዋረት በዓለም ስመ-ጥር በሆኑት የሮያል ኖርዌጂያን የባህር ኃይል

---

[6] Yohannes, Esrael. "The Expansion of Military Bases in the Horn of Africa: Analysis of Its Challenges and Opportunities to Ethiopia's Policy in the Region." Thesis Submitted in Partial Fulfilmentof the Requirements for the Degree of Masters of Art in International Relations and Diplomacy. Addis Ababa University, 2018.

[7] Horton, M. Hot Issue - The Race for Bases, Ports, and Resources in the Horn of Africa Heats Up – Jamestown Foundatin. 11 October 2019. https://jamestown.org/program/hot-issue-the-race-for-bases-ports-and-resources-in-the-horn-of-africa-heats-up/, Accessed on 3 January 2023

[8] Berg, W and Meeste, J. "Ports & Power: the Securitisation of Port Politics." Clingendael. 2018. https://www.clingendael.org/sites/default/files/2018-05/Ports_and_Powers.pdf, Accessed on 3 January 2023

ኮሌጅ፣ የብሪትሽ ሮያል ባህር ኃይል ኮሌጅ፣ የጣሊያን ናቫል አካዳሚ፣ የዩናይትድ ስቴትስ ናቫል አካዳሚ፣ የሶቭየት ናቫል አቪዬሽን፣ እና በሌሎችም ታዋቂ የባህር ኃይል መኮንኖች አካዳሚዎች የኢትዮጲያና የኤርትራ ተወላጆች በከፍተኛ ቁጥር እየተላኩ ትምህርት ቀስመው በአማካሪነት እና በአሠልጣኝነት ሀገራቸውንና ሕዝባቸውን እንዲያገለግሉ አድርጓል።

በአሁኑ ሠዓት በአዲስ አበባ፣ ሽሮ ሜዳ አካባቢ የሚገኘው የቀድሞው የኢትዮጲያ መንግሥት የባህር ኃይል ዋና የጦር ሠፈር (ማለትም በአሁኑ ሰዓት የምሥራቅ አፍሪካ ተጠባባቂ ብርጌድ ዋና ማዘዣ ጣቢያ) ዋና መቀመጫ ሆኖ እያገለገለ የሚገኝ ሲሆን ብዙዎቹ መርከቦች እንደወደሙ የቀሩትም ለሌሎች ሃገሮች እንደተሸጡ ሌሎቹም ባሉበት በስብሰው ቀርተዋል።

የኢትዮጲያ ሮያል የባህር ኃይል በስም ተለይተው የሚታወቁ በርካታ የጦር መርከቦችና ጀልባዎች የነበሩት ሲሆን ለኢትዮጲያ በህይወት የተረፈቻት አንዲት ጂቢ-21 የተሰኘች ብቸኛ የቅኝት የጦር ጀልባ በአሁኑ ሰዓት በኢትዮጲያ መከላከያ ሠራዊት ባለቤትነት በጣና ኃይቅ ላይ እንደምትገኝ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

የቀድሞው የኢትዮጲያ የባህር ኃይል አባላት እንደገለጹት የኢትዮጲያ ባህር ኃይል ከዓለም ተደናቂ ሃይሎች አንዱ እንደነበረ እና ሶስቱንም የዓለም ውቅያኖሶች ያቋረጠ ትልቅ የባህር ኃይል ነበር። ከወደብ ጠባቂ (ኮስት ጋርድ) ጀምሮ እስከ ትልቁ የጦር ሚሳኤል ድረስ ታጥቆ ይንቀሳቀስ የነበረ ኃይል ነው ሲሉ ይገልፁታል። በ1947ዓ.ም ተቋቁሞ በደርግ ዘመን እስከ 3ሺ ድረስ የተማረና የሰለጠነ የሰው ኃይል የነበረው በ1983 ምጽዋ በኤርትራ ነጻ አውጪ ግንባር ከተያዘበት ጀምሮ ህልውናው ይስለመለም እንደገባ ታሪክ ይናገራል። በ1983 ዓ.ም. የኢህአዴግ ሠራዊት የደርግን መንግስት አሸንፈው የመንግስት ለውጥ ከተደረገ በኋላ የኢትዮጲያ ባህር ኃይል ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ህልውናው አክትሞ እንዲፈርስ ተደረገ።

## 3. ባህር በር ሳይኖራቸው ራሱን የቻለ የባህር ኃይል ያቋቋሙ ሃገራት

በዓለማችን ላይ ውስን ሃገሮች የባህር በር ሳይኖራቸው ነገር ግን በአደረጃጀት ደረጃ ራሱን የቻለ ባህር ኃይል ያቋቋሙ አሉ። እነዚህም ሃገሮች በዋነኝነት በሃገር ውስጥ ባላቸው ወንዞች ወይም ሃይቆች የሚሰጣቸውን ተልዕኮ የሚፈፅሙ ናቸው። በምሳሌነት ከሚጠቀሱት ሃገሮች ውስጥ አይዘርባይጃን፣ ቦሊቪያ፣ ሴንትራል አፍሪካ ሪፐበሊክ፣ ላኦስ፣ ሩዋንዳ እና ፓራጓይ ናቸው። እነዚህ ሃገሮች ባህር ኃይል ሲያቋቁሙ መሰረታዊ የሚባሉት ተልዕኮዎቻቸው፤ የውስጥ ወይንም ድንበር ተሻጋሪ የሆኑ ትላልቅ ወንዞችንና ሃይቆችን ቅኝት ለማድረግ፣ የድንበር እና የሃይቅ መብት ማስጠበቅ፣ ከአንድ አገር ወደ ሌላ አገር የሚደረግን ህግ ወጥ ስደት እና ፍልሰት ለመከላከል፣ እና ህገወጥ ንግድ (ኮንትሮባንድ)፣ የመሳሪያ ዝውውር፣ የገንዘብ ዝውውር፣ የአሳ ማስገር፣ የአደንዛዥ ዕፅ ዝውውር የመሳሰሉትን ለመቆጣጠር ነው።

### 3.1 በእግረኛ ሰራዊት ውስጥ ተደርቦ የሚኖር ባህር ኃይል

በዓለማችን በአደረጃጀት ራሱን የቻለ ባህር ኃይል ሳይኖራቸው ነገር ግን በሃገራቸው መከላከያ ኃይል ወይም በእግረኛ ሰራዊት ስር ሆነው በትላልቅ ወንዞች ወይም በሰፋፊ ሃይቆች ላይ ከዋናው ሰራዊት በክንፍ/ቅርንጫፍ ደረጃ ክፍል ኖሯቸው የሚንቀሳቀሱ የውሃማ አካላት ላይ ግዳጅን መወጣት የሚችሉ ዩኒቶች ያላቸው ሃገሮች አሉ። ከነዚህም ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ሃገሮች ቡሩንዲ፣ ሃንጋሪ፣ ኡጋንዳ፣ ማላዊ እና ማሊ፣ ስዊዘርላንድና ኡዝቤኪስታን ተጠቃሽ ናቸው።

### 3.2 ያለ ባህር በር ራሱን የቻለ ባህር ኃይል

የዚህ አይነቱ ባህር ኃይል የባህር በር የሌለው ነገር ግን በአደረጃጀት ደረጃ ራሱን የቻለ ባህር ኃይል ኖሮት ተልዕኮውን ከሌሎች የባህር በር ካላቸው ሃገራት ባህር ኃይል ጋር በጣምራ ተልዕኮውን የሚወጣ ነው። ይህ አይነቱ የባህር ኃይል በኤስያ እና በአውሮፓ ሃገራት የተለመደ ሲሆን የባህር በር ሳይኖራቸው የባህር ኃይል አቋቁመው ከጎረቤቶቻቸው ወይም ከአጋሮቻቸው ጋር በጋራ የሚሰሩ የባህር ሃይሎች ብዙ ናቸው። ለምሳሌ ብዙዎቹ የቀድሞው የሶቪየት ህብረት አባል ሃገራት ከራሺያ ጋር አብረው ይሰራሉ። ለምሳሌ ቤላሩስን መውሰድ እንችላለን። በአውሮፓም በተመሳሳይ ባህር በር የሌላቸው ሃገራት ከሌሎች ጋር በመሆን የዓለም አቀፉን የባህር መብቶቻቸውን ያስጠብቃሉ። ለንግድ መርከቦቻቸው የጥበቃ አገልግሎት ይሰጣሉ።

### 3.3 የባህር በር ያለው ሃገር ባህር ኃይል

በዓለማችን ያሉ በርካታ ሃገራት ለባህር ወይም ለውቅያኖስ ተጎራባች ናቸው። እነዚሁ ሃገራት አደረጃጀቱ፣ መጠኑ፣ ግዝፈቱ፣ አቅም እና አሰላለፉ ይለይ እንጂ ከሞላ ጎደል ሁሉም የባህር ኃይል አላቸው። ብዙዎቹም ከወታደራዊ ወይም መከላከያ ሃይላቸው ስር እንደ አንድ አደረጃጀት የራሱ የሆነ አደረጃጀት አለው። በዓለማችን ግዙፍ እና ጠንካራ የባህር ኃይል ካላቸው ሃገራት መካከል ዩናይትድ ስቴትስ፣ ሩሲያ፣ ቻይና፣ ዩናይትድ ኪንግደም፣ ፈረንሳይ፤ ጣልያን፤ ጀርመን ይገኙበታል። የነዚሁ ሃገራት የባህር ኃይል በከፍተኛ ትልልቅ የጦር መረከቦች (የውጊያ ጀቶችንና ሄሊኮፕተሮችን የሚሸከሙና የሚያንደረድሩ የጦር መርከቦች)፣ ሰርጓጅ መርከቦች፣ የቅኝት ጀልባዎች፣ ብዙ ባህረኞች... ወዘተ የተደራጀ ነው። ከአፍሪካ ደቡብ አፍሪካ፣ ግብፅ እና አልጄሪያ ግዙፍ የባህር ኃይል ያላቸው ሃገራት ናቸው።

## 4. የአፍሪካ ቀንድ ጂኦ-ፖለቲካዊ ሁኔታ

በዓለም አቀፍ ደረጃ የአፍሪካ ቀንድ የቀይ ባህር እና የሰሜን ህንድ ውቅያኖስ አካባቢ የሚገኝ ዋነኛ ዓለም አቀፍ የባህር ንግድ እንቅስቃሴ የሚካሄድበት አካባቢ ነው። በቀጠናው ኤርትራ፥ ጅቡቲ፥ ሱዳን፥ ደቡብ ሱዳን፥ ኢትዮጲያ፣ ኬኒያ እና ሶማሊያ ይገኛሉ። ይህ ቀጠና በየዓመቱ ከ700 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር በላይ የንግድ ልውውጥ የሚደረግበት ከመሆኑም በላይ ሜድትራኒያን ባህር፣ የስዊዝ ቦይና ቀይ ባህርን ከህንድ ውቅያኖስና ምዕራባውያን ገበያዎችን ከእስያና ከመካከለኛው ምስራቅ ገበያ ጋር በማገናኘት ትልቅ የንግድ መተላለፊያ ሆኖ ያገለግላል።[9] ቀጠናው ከ2500 ማይል በላይ የባህር ዳርቻ ያለው በመሆኑና በቅርብ ርቀት የአረብ ሀገራት የሚገኙበት ነው። አካባቢው ከትናንሽ ሀገር በቀል የፖለቲካ ሽኩቻ እስከ ቀጠናዊ እና ዓለም-አቀፋዊ የፖለቲካ ሽኩቻና ፉክክር የሚካሄድበት ሰላም አልባ የግጭት ቀጠና በመሆኑ አሸባሪ ቡድኖች እና የባህር ላይ ወንበዴዎች እንደፈለጉ እንዲንቀሳቀሱ እና እንዲፈነጩ እድል የሚሰጥ ነው።[10]

የአፍሪካ ቀንድ ለመካከለኛው ምስራቅና እስያ ባለው  ቅርበት እና በቀይ ባህር አካባቢ ካሉ ስጋቶች በመነሳት ከሌላ ጊዜ በተለየ መልኩ ባለፉት ሁለት አስር አመታት ከፍተኛ የሆነ የሃገሮች ተሳትፎና የግዳጅ ስምሪቶች የታዩበት ነው። በተለይ ደግሞ ቀጠናዊ እና ዓለም አቀፋዊ የፀጥታ ተቋማት በከፍተኛ ሁኔታ ተልዕኮ እየፈፀሙ ይገኛሉ።[11] በርካታ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት አብዛኞቹ ሃገራትና የፀጥታ ተቋማት በቀጠናው ላይ መታየት የጀመሩት ከ2001 እ.ኤ.አ የአል-ቃይዳ የሽብር ጥቃት በአሜሪካ መንትዮች ህንፃ ላይ ተከስቶ የበርካታ ሺዎችን ህይወት ከቀጠፈ በኋላ ነው።

በአፍሪካ ቀንድ የግሎባል ሃይሎች (በዋነኝነት አሜሪካ፣ ቻይና እና ሩሲያን ይመለከታል) በቀጠናው ከፍተኛ የሆነ ወታደራዊ ሽኩቻ ውስጥ ሆነው ቀጠናው ላይ ወታደራዊ ካምፖቻቸውን በመገንባት ቀጠናው ከፍተኛ የሆነ ወታደራዊ ውድድር እንዲኖረው እያደረጉ ይገኛሉ። በተመሳሳይ ቀጠናዊ ሃይሎች እና ዓለምአቀፍ ጥምር ሃይሎች በቀጠናው ላይ በሚደረገው የሚሊታራይዜሽን እድገት ሚናቸው እጅግ የጎላ ነው።


## 4.1 ግሎባልና ቀጠናዊ ሃይሎች ቅርምት በአፍሪካ ቀንድ

በአፍሪካ ቀንድ የሚገኙ ሃገራት ከኢትዮጲያና ደቡብ ሱዳን በስተቀር ሁሉም የራሳቸው የባህር በር ያላቸው በመሆኑ የባህር ኃይልም ካደራጁ ዓመታትን አስቆጥረዋል። በጂቡቲ የተለያዩ ሃገራት ወታደራዊ ቤዝ አላቸው። ከነዚህም አሜሪካ፣ ፈረንሳይ፣ ጣሊያን፣ ጃፓን፣ ቻይና እና ሳውዲ አረቢያ ዋና ዋናዎቹ ናቸው። የተወሰኑ ሃገራት በጂቡቲ ወታደራዊ ቤዝ ባይኖራቸውም ቀደም ብለው ቤዝ ባቋቋሙ ሃገሮች ካምፕ ላይ በተደራቢነት በቀጠናው ላይ ህልውናቸውን ያረጋገጡም አሉ። ለምሳሌ በፈረንሳይ ወታደራዊ ቤዝ በተደራቢነት ወታደራዊ ቤዝ የከፈቱ ሃገሮች ጀርመንና ስፔይን ሲሆኑ፤ በአሜሪካ ወታደራዊ ቤዝ እንግሊዝ እና በጃፓን ወታደራዊ ቤዝ ህንድ ይገኛሉ።

[9] Questions over foreign military presence in Africa - ISS Africa. https://issafrica.org/pscreport/psc-insights/questions-over-foreign-military-presence-in-africa

[10] Ibid.

[11] Melvin, Neil. The Foreign Military Presence in the Horn of Africa Region. SIPRI. 2019. https://www.sipri.org/sites/default/files/2019-05/sipribp1904_1.pdf




*ምስል 1. በአፍሪካ ቀንድ የሚገኙ የተለያዩ ሃገራት ወታደራዊ ቤዞች*

በጂቡቲ ወታደራዊ ቤዝ ያላቸው ሃገሮች በዋናነት በቀጠናው የሚወጧቸው የግዳጅ አይነቶች እንደየ ሃገራቱ ብሄራዊ ጥቅም የሚለያይ ነው። ሃገራቱም ለየግዳጃቸው አመቺ ነው የተባለውን አደረጃጀትና መዋዕለ ንዋይ የሚያዘጋጁ ቢሆንም ዋና ዋና የሚባሉ ተልዕኮዎቻቸውን እንደሚከተለው ማየት ይቻላል። ፀረ-የባህር ላይ ውንብድና (ቀይ ባህር፣ የኤደን ባህረ-ሰላጤ እና አረብ ባህር) - Anti-Piracy (Red Sea, Gulf of Aden and Arabian Sea፣ ሰብዐዊ ድጋፍ - Humanitarian Aid Mission፣ የሰላም ማስከበር ተልዕኮ - Peacekeeping Mission፣ ታክቲካል እና ስትራቴጂክ ወታደራዊ ዘመቻዎች - Tactical & Strategic Military Operations፣ የፀረ-ሽብር ዘመቻ (በየመን እና በአፍሪካ ቀንድ) - Anti-terror Operations Combat terrorist (Yemen & Horn of Africa)፣ መረጃ - Intelligence፣ ቁጥጥር - Survillence። በጂቡቲ ወታደራዊ ቤዝ ያላቸው ሃገሮች እጅግ ግዙፍ መዋዕለ ንዋይ አፍስሰው እና በርካታ የሰው ኃይል አሰማርተው በቀጠናው ላይ በመሆን የተለያዩ ግዳጆችን እንደሚወጡ ማየት ይቻላል። ከዚህ በታች ያለው ሰንጠረዥም የሚያሳየን ማን የት ምን እና ከመቼ ጀምሮ የሚሉትን ማየት ጉዳዩን የበለጠ በጥልቀት ለመረዳት ያግዛል።

| አገር | የሚገኝበት አገር | የግዳጅ አይነት | የተመሰረተበት ጊዜ |
|---|---|---|---|
| ቻይና | ጂቡቲ | ወታደራዊ ቤዝ፣የባህር ኃይል ቤዝ እና የሄሊኮፕተር ማረፊያ | 2017 |
| ፈረንሳይ | ጂቡቲ | ወታደራዊ ቤዝ፣የባህር ኃይል ቤዝ እና የአየር ቤዝ | 1977 |
| ጀርመን | ጂቡቲ | ወታደራዊ ቤዝ፣እና የአየር ቤዝ | 2001 |
| ጣሊያን | ጂቡቲ | ወታደራዊ ቤዝ፣እና የአየር ቤዝ | 2013 |
| ጃፓን | ጂቡቲ | ወታደራዊ ቤዝ፣እና የአየር ቤዝ | 2011 |
| ሳኡዲ አረቢያ | ጂቡቲ | ወታደራዊ ቤዝ | 2015 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ስፔይን | ጂቡቲ | ወታደራዊ ቤዝ፣እና የአየር ቤዝ | 2008 |
| ኢመሬትስ | ጂቡቲ | ወታደራዊ ቤዝ | 2015 |
| አሜሪካ | ጂቡቲ | ወታደራዊ ቤዝ፣እና የአየር ቤዝ | 2001 |
| እስራኤል | ኤርትራ | ወታደራዊ ቤዝ | በውል ያልታወቀ |
| ኢመሬትስ | ኤርትራ | ወታደራዊ ቤዝ፣የባህር ኃይል ቤዝ እና የአየር ቤዝ | 2015 |
| ቱርክ | ሶማሊያ | ወታደራዊ ቤዝ (ሞቃዲሾ) | 2017 |
| ኢመሬትስ | ሶማሊያ | ወታደራዊ ቤዝ (ሞቃዲሾ) | 2015-2018 |
| ኢመሬትስ | ሶማሊያ | ወታደራዊ ቤዝ (ሶማሊላንድ) | 2019 |
| እንግሊዝ | ሶማሊያ | ወታደራዊ ቤዝ (ሞቃዲሾ) | 2017 |
| አሜሪካ | ሶማሊያ | ወታደራዊ ቤዝ፣እና የአየር ቤዝ | 2016 |
| አሜሪካ | ኬኒያ | ወታደራዊ ቤዝ፣እና የአየር ቤዝ | 2006 |

*ሰንጠረዥ 2. በአፍሪካ ቀንድ የሚገኙ የተለያዩ ሃገራት ወታደራዊ ቤዞች አቅም*[12]

### 4.2 ዓለም አቀፍ ሃይሎች በቀይ ባህር እና በኤደን ባህረ-ሰላጤ

በአፍሪካ ቀንድ እና በቀጠናው ባሉ ውሃማ አካሎች እና በቅርብ ርቀት በሚገኙት አረብ ሃገሮች አካባቢ በርካታ ዓለም አቀፍ ወታደራዊ ግዳጆችን የሚወጡ ተልዕኮች አሉ። እነዚህም ግዳጆች በዓለማችን በታወቁ የፀጥታ እና የደህንነት ተቋማት እና በሃያላን አገራት የሚመሩ ናቸው። የግዳጅ አይነታቸውም በዋናነት የባህር ላይ ደህንነት፣ ፀረ-ሽብር፣የባህር ላይ ውንብድና ወዘተ የመከላከል ሲሆን በአየር፣ በስፔስ፣ በሳይበር እና በውሃ ላይ የታገዘ ተልዕኮን የሚፈፅሙ ናቸው። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም የመሬት ላይ ስፔሻል ኦፕሬሽኖችን በተናጥል እና በጆይንት ያከናውናሉ።

| የተልዕኮው መጠሪያ | የሚገኝበት ቦታ | የተመሰረተበት ጊዜ | ተሳታፊዎች |
|---|---|---|---|
| ጥምር ግበረ-ኃይል -150 ፣ ጥምር የባህር ሃይሎች፣ የባህር የደህንነት ዘመቻ እና ፀረ-ሽብር | ቀይ ባህር፣የኤደን ባህረ-ሰላጤ፣የኦማን ባህረ-ሰላጤ እና ህንድ ውቅያኖስ | 2002 | በአሜሪካ መሪነት፣ የ33 አገሮች ጥምረት |
| ጥምር ግበረ-ኃይል -152 ፣ የባህር የደህንነት ዘመቻ | በሰላጤው አካባቢ | 2004 | በአሜሪካ መሪነት፣ የ33 አገሮች ጥምረት |
| አትላንታ ኦፕሬሽን | ባኤደን ባህረ-ሰላጤ፣ ቀይ ባህር በሶማሌ ሰርጥ | 2008 | አውሮፓ ህብረት እና ሌሎች ተባባሪ ሃገሮች |

[12] Melvin, Neil. The Foreign Military Presence in the Horn of Africa Region. SIPRI. 2019. https://www.sipri.org/sites/default/files/2019-05/sipribp1904_1.pdf

| | | | |
|---|---|---|---|
| ጥምር ግበረ-ኃይል -151 ፣ የባህር የደህንነት ዘመቻ | ባኤደን ባህረ-ሰላጤ እና በሶማሌ ሰርጥ | 2009 | በአሜሪካ መሪነት፣ የ33 አገሮች ጥምረት |
| ኦፕሬሽን ኦሽን ሺልድ | በኤደን ባህረ-ሰላጤ ፣ህንድ ውቅያኖስ እና ሰላጤው | 2009-2016 | የኔቶ አባል ሃገሮች |
| የአውሮፓ ህብረት የስልጠና ተልዕኮ በሶማሊያ | ሶማሊያ | 2010 | አውሮፓ ህብረት እና ሌሎች ተባባሪ ሃገሮች |

*ሰንጠረዥ 3. በአፍሪካ ቀንድ የሚገኙ ዓለም-አቀፍ ወታደራዊ ግዳጆች*

## 4.3 የቀጠናዊ እና ዓለም አቀፋዊ ሃይሎች ቅርምት በቀጠናዊ የሚኖረው እንድምታ

በቀጠናው ላይ የሚኖረው ወታደራዊ ሃይሎችን የማብዛት ርብርብ የራሱ የሆነ ጠቀሜታ እና በዛው ልክ በርካታ ስጋቶችን ይዞ ይመጣል። የወታደራዊ ሃይሎች አሰላለፍ ይዞት የሚመጣው ስጋት እና ተስፋ በሶስት ዋና ዋና ዘርፎች ይመደባሉ። እነሱም በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ እና በፀጥታ መስክ እንደሚታዩ የተለያዩ ምንጮች ያስረዳሉ።

በፀጥታ፤ በፀጥታ በኩል የወታደራዊ ሃይሎች በቀጠናው መስፋፋት በርካታ የሆኑ ጠቀሜታዎች አሉት። በቀጠናው ያሉ የፀጥታ ጉዳዮችን በተመለከተ ወቅታዊ እና በቴክኖሎጂ ተደግፈው የተሰበሰቡ የመረጃ ልውውጥ ለማድረግ ያግዛል፤ በቀጠናው ላሉ ሃገራት የፀጥታ ጉዳይ ላይ የሚያፈሱትን መዋዕለ ንዋይ እና ጊዜ በመቆጠብ በውስጥ ጉዳያቸው ላይ ብቻ እንዲያተኩሩ ያግዛል፤ ቀጠናው የተረጋጋ ፀጥታ እንዲኖረው በማድረግ በኩል ከፍተኛ አስተዋፅ አለው፤ በቀጠናው ላይ እየተስፋፋ ያለው ኃይል በአብዛኛው የባህር ኃይል በመሆኑ ለቀጠናው ሃገራት የባህር ኃይላቸውን በማሳደግ በኩል ከፍተኛ ድጋፍ ያደርጋል። እንዲሁም የምድር እና አየር ሃይሎች ጋር የተሻለ ወታደራዊ ትብብር ለመፍጠር እና የልምድ ልውውጥ በማድረግ ዘመቻዎችን በጋራ ለመወጣት ያስችላል። በአጠቃላይ በወታደራዊ መስኩ ቴክኒካዊና ቁሳዊ ድጋፍ፣ የተግባር ልምምዶች እና የእውቀት ሽግግር በማድረግ በኩል ከፍተኛ ሚና አላቸው።

የሃያላን በአፍሪካ ቀንድ የሚያደርጉት የሚሊታራይዜሽን አሽቅድድም ከፀጥታ አንፃር በርካታ ተስፋዎችን ቢያመጣም ቀላል የማይባሉ ስጋቶችም አሉት። በትብብር ለመስራት በሚደረገው ሂደት ውስጥ በቀጠናው ያሉ ሃገሮች ወታደራዊ አቅሞቻቸውን በሙሉ አሳልፈው ለሶስተኛ ወገን መረጃ እንዲሰጡ ያደርጋቸዋል። ይህም ለሌላ ጠላት ተላልፎ መረጃ እንዲተላለፍ በር ይከፍታል፤ ቀጥተኛ ባላሆነ መንገድ በተለያዩ ዋርፌሮች በመጠቀም በመከላከያ ሲስተሙ ላይ ጫና ሊያሳርፉ ይችላሉ፤ በአቅራቢያ የሚገኙ የውጪ ሃይሎች በመሆናቸው በአገራቱ የውስጥ ጉዳዮች ላይ ሊገቡ ይችላሉ። ወይንም ለተቃራኒ ሃይሎች ወታደራዊ ድጋፍ በማድረግ ጉዳት ሊያመጡ ይችላሉ። አንዳንዴም በጠላትነት ከተፈረጁ ሶስተኛ ወገን ጋር ሊያብሩ ይችላሉ፤ ሃገራቱ በራሳቸው አቅም እና ፍላጎት ላይ ተመስርተው መከላከያቸውን እንዳይገነቡ ጫና ሊያደርጉ ይችላሉ። ወይንም በሌላ አባባል ጥገኝነትን ያላብሳሉ።

በፖለቲካ፤ በቀጠናው ላይ እየተስፋፋ ያለው የወታደራዊ ሃይሎች ካምፕ እና የተለያዩ ዘመቻዎችን ማቋቋም በፖለቲካውም መስክ ስጋትና ተስፋዎችን ይዞ ሊመጣ ይችላል። በፖሊቲካው መስክ ሊከሰቱ ከሚችሉት ዋና ዋና ስጋቶች መካከል፡- በሃያላኑ መካከል በሚደረገው የበላይነትን የማረጋገጥ ሽኩቻ ቀጠናውን የበለጠ ወታደራዊ መናኸሪያ በማድረግ ለህገወጥ የመሳሪያ ዝውውር እና ሽያጭ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፤ በሃገሮች መካከል ያለውን በንግግር ሊፈቱ የሚችሉ ቅራኔዎች እና አለመግባባቶች የበለጠ የማካረር እድል ይኖረዋል፤ ቀጠናው ለወታደራዊ ሃይሎች መናኸሪያ በማድረጉ ሂደት በተለይ ሃያላኑ በበዙ ቁጥር የኢትዮጲያን በቀጠናው ያላትን ተሰሚነት እና ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ቀስ በቀስ ይቀንሳል።

ኢኮኖሚ፤ የአፍሪካ ቀንድን እና አካባቢውን ወታደራዊ ሃይሎችን በማብዛት የመቆጣጠሩ ሂደት በኢኮኖሚውም ዘርፍ ቀላል የማይባል ተስፋዎች እና ስጋቶች አሉት። ኢትዮጲያ ከ90 በመቶ በላይ የሚሆነው የወጪ እና ገቢ ንግድ እንዲሁም ከ11 በላይ በሚሆኑ የንግድ መርከቦቻችን አማካኝነት በቀጠናው ላይ በቋሚነት ይንቀሳቀሳል።ስለዚህም በቀጠናው ላይ ያሉ ወታደራዊ ሃይሎች ከስጋት ነፃ የንግድ መስመርና ቀጠና በመፍጠር እንቅስቃሴውን በማሳለጥ በኩል ሚናቸው የጎላ ነው። የንግድ መርከቦቻችንን ከባህር ላይ ውንብድና በመጠበቅ ለትልቁ ኢኮኖሚ ያላቸው ድጋፍ እጅግ የላቀ ነው። ሃያላኑ ለራሳቸው የሚገነቡት መሰረተ ልማት ለሃገራችንም ለቀጠናውም እድገት ጠቀሜታ ይኖረዋል። በኢኮኖሚው መስክ ሊኖሩ የሚችሉት

[13] Melvin, Neil. The Foreign Military Presence in the Horn of Africa Region. SIPRI. 2019. https://www.sipri.org/sites/default/files/2019-05/sipribp1904_1.pdf

ስጋቶችን በተመለከተ ዋና ዋናዎቹ እንደሚከተሉት ይገለፃሉ። በሃያላኑ ጣልቃ ገብነት የተነሳ የኢምፖርትና ኤክስፖርት ዋጋ ጫና ሊፈጠርበት ይችላል። በቀጠናው ላይ ካሉ ሃገሮች ጋር በኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ ኢትዮጲያ በሚኖራት ፍላጎት ላይ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ሃገራቱ ጣልቃ በመግባት የሶስተኛ ወገን ጫና ሊያሳድሩ ይችላሉ።

## 5. የባህር ኃይል እና የኢትዮጲያ ብሔራዊ ደህንነት

### 5.1 የባህር ኃይል አስፈላጊነት የባህር በር ለሌላቸው ሃገራት እንዲሁም ለኢትዮጲያ

ብዙ ሃገራት የባህር ኃይል የሚያቋቁሙት የባህር ወሰን/ድንበር ወይም የባህር ክልላቸውን ለማስጠበቅ ከዚህም ሲያልፍ ዓለም-አቀፋን የባህር ደህንነት ለመጠበቅ፤ ለትላልቅ የጦር መሳሪያ ሽያጭና እና ማጓጓዣነት፤ የመሳሪያ ሽያጭ ዝውውር ቁጥጥር ለማድረግ፤ የባህር ላይ ውንብድናን ለመከላከል፤ የንግድ መርከቦቻቸውን ደህንነት ለማስጠበቅ፤ በምድር አካል ላይ በመሆን ሊመከቱ የማይችሉ የጠላት እንቅስቃሴን ለመመከት፤ በዓለም-አቀፉ የባህር ክልል ላይ ለሚደረጉ የተፈጥሮ ሃብት ጥበቃና ልማት ላይ ለመሰማራት፤ የባህር ላይ ህገ-ወጥ የሰው ዝውውር ለመቆጣጠር ነው።

ከባህርና ውቅያኖስ ባሻገር ደግሞ በሁለት ወይም በሶስት ሃገራት መካከል (በአህጉር ውስጥ) የተዋሳኝ የውሃ አካላት ያለ የባህር ወይም የውሃማ አካላት የወሰን ጥበቃ እና ፍትሃዊ የሆነ የውሃ ሃብት አጠቃቀም መብትን ለመጠበቅ የባህር ኃይል አስፈላጊ ነው። የባህር ዳርቻ ያላቸው ሃገራት የባህር ድንበር የሚባለው እስከ 12 ኖቲካል ማይል (22.22400 ኪሎ ሜትር) ድረስ ብቻ ያለው እንደሆነ የዓለም-አቀፉ ህግ ይደነግጋል። ከዚህ ኪሎ ሜትር ባሻገር ያለው ያለም አቀፍ የባህር ክልል ነው። በዚህም ክልል ውስጥ ማንኛውም ሉዓላዊ ሃገር በነፃነት የመንቀሳቀስ፣ ከባህሩም የመጠቀም መብት አለው።[14]

ኢትዮጲያ የባህር ክልል ባይኖራትም ከላይ ከተጠቀሱት ከአንዱ ግዳጅ በስተቀር (የባህር በር ወይም የባህር ወሰን ክልል ለማስጠበቅ ከሚለው በስተቀር) ሁሉም ልትከውናቸው የሚገቡ መብቶች፣ ግዴታዎችና የሚጠበቁ ድርሻዎች ናቸው። የየሀገራቱ የባህር ኃይል ፍላጎት እና ተልዕኮ እንዳሉበት ቀጠናዊ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ቢሆንም ዋናው ማጠንጠኛ ግን ጥቅምን መሰረት ያደረገ ነው። በአንድ ወቅት የኢፌዲሪ. የባህር ኃይል አዛዥ ሬር አድሚራል ክንዱ ገዙ እንደገለጹት አሁን ባለው ሁኔታ ዘጠና ከመቶ በላይ የሚሆነው የኢትዮጲያ ገቢና ወጪ ንግድ የሚሳለጠው በውሃ ላይ በሚደረግ ጉዞ መሆኑን እና በተለይም እ.ኤ.አ. ከ2008 እስከ 2010 በምስራቅ አፍሪካ የነበረውን የባህር ላይ ውንብድና አስቸጋሪነት አውስተዋል።

እንደአሳቸው ገለጻ እንደዚህ ዓይነት የሀገራትን ጥቅም የሚጎዱ ውንብድናዎችን ለመከላከል የባህር ኃይል ወሳኝ እና ብቸኛው መንገድ ነው። ምክንያቱም አሁን ባለው ዓለም-አቀፍ ሁኔታ በአንድ ቀጠና የሚፈጠር ችግር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ዓለም-አቀፋዊ ችግር እየሆነ እየታየ ነው። በሌላ አገላለፅ ሬር አድሚራሉ ያነሱት ነጥብ ኢትዮጰያ ያሏትን የንግድ መርከቦችና ለሀገር ያላቸውን ፋይዳ ነው። በወቅቱ የአስራ አንድ የንግድ መርከቦች ባለቤት የሆነችው ኢትዮጲያ ሰንደቅ አላማዋን እያውለበለቡ ከአህጉር አህጉር የሚዘዋወሩት መርከቦቿ ደህንነት ተጠብቆ በሰላማዊ ሁኔታ ስራቸውን ለማከናወን አስተማማኝ ጥበቃ ሊደረግላቸው ይገባል ለዚህም በዘርፉ የሰለጠነ የባህር ኃይል መኖር እንደሚያስፈልግ ይገልፃሉ።

ኢትዮጲያ 90 በመቶ የሚሆነው የውጭ ንግድ በቀይ ባህርና በኤደን ባህረ-ሰላጤ ላይ የተመሰረተ ከመሆኑም በላይ የሃገሪቱ የኢንተርኔት ግንኙነት ዋና ፋይበር ኦፕቲክስ (Fiber Optics) የሚያልፈውም በዚሁ ክልል ነው። በነዚህ አበይት ምክንያቶች ኢትዮጲያ ሰፊ ብሔራዊ የደህንነት ፍላጎት ያላት በመሆኑ የባህር ሀይል ለማቋቋም የአቅም ማሰባሰብና ስልጠና ስራዎችን እያከናወነች ነው። ስለ ባህር ኃይል አስፈላጊነት በአንድ ወቅት የኢትዮጲያ የባህር ኃይል ዋና አዛዥ ሬር አድሚራል ክንዱ ሲናገሩ "በኢትዮጲያ ከውስጥ እና ከውጪ የሚቃጡ ጥቃቶችን የሚመክት ባህር ኃይል እየተገነባ ነው። የሀገርን ደህንነት ማስጠበቅ የሚችል፣ ከውስጥ እና ከውጭ የሚመጡ ችግሮችን የሚመክት ዘመናዊ ባህር ኃይል መገንባትና ማሰልጠን አስፈላጊ ነው።"[15] በአንድ አጋጣሚ ዋና አዛዡ ለባህር ኃይል ተሟሪዎች ባስተላለፉት መልዕክት "ኢትዮጲያ ከባህር ኃይል ማግኘት የምትችለውን ጥቅም እንድታገኝ በሀገር ውስጥና በተለያዩ የውጭ ሀገራት የሚሰጣቸውን ሥልጠና በብቃት መወጣት ይገባቸዋል"[16] ማለታቸውንም ከመከላከያ ሰራዊት የተገኘው መረጃ ያመላክታል። የባህር ኃይል ከማቋቋም አስፈላጊነት ጋር በተያያዘ የኢፌዲሪ መከላከያ ሰራዊት ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም የነበሩት ጄነራል ሰዓረ መኮንን "...ሃገራችን በአዲሱ ዓመት ባህር ኃይሏን ታደራጃለች። ሀገራችን ያለችበት ቀጠና ስትራቴጂያዊ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የተለያዩ አካላት የሚያደርጉት

---

[14] United Nations Convention on the Law of the Sea. https://www.un.org/depts/los/convention_agreements/texts/unclos/part2.htm

[15] በኢትዮጵያ ከውስጥ እና ከውጪ የሚቃጡ ጥቃቶችን የሚመክት ባህር ኃይል እየተገነባ ነው - የባህር ኃይል ዋና አዛዥ - Fana Broadcasting Corporate S.C. https://www.fanabc.com/archives/120764

[16] ዝኒ ከማሁ

እንቅስቃሴ ችላ እንደማይባል ነው። የባህር ኃይሉ መቋቋም ያለውን አካባቢያዊ ተጽዕኖ ለመመከት በመንግስት ታምኖበታል" በማለት ገልጸዋል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ የሰራዊቱን አቅም ለማጎልበትም የአራተኛው ትውልድ ቴክኖሎጂን መሰረት ያደረገ ግንባታ እንደሚካሄድ ገልጸው ለዚሁ የሚያግዝ የስርዓተ-ትምህርት ቀረፃና የሪፎርም ስራዎች በስፋት እየተሰራ መሆኑን ገልፀዋል።[17] የቀድሞውን የሃገር መከላከያ ሰራዊት ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም ሰዓረ መኮንንን የሚደግፍ ሃሳብ በተመሳሳይ በአሁን ግዜ የመከላከያ ሰራዊት ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም የሆኑት ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ኢትዮጲያ ባህር ሃይል ልታቋቁም መሆኑን በመግለጽ ሲያስረዱ "የኢትዮጲያ መከላከያ ሰራዊት ቀደም ሲል ባህር ኃይል የነበረው እንደሆነ ጠቁመው የባህር በር የለንም በሚል አስተሳሰብ እንደፈረሰ አስረድተዋል። አሁን ግን ዘመናዊና ጠንካራ ጦር ኃይል ለመገንባት እቅድ ስለተያዘ ኢትዮጲያ ባህር ኃይል ያስፈልጋታል ተብሎ መወሰኑን ገልፀዋል። የባህር ሃይሉ በቀይ ባህርና ህንድ ውቅያኖስ አቅራቢያ የጦር ሰፈር እንደሚኖረውም ጠቁመዋል። የጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ አመራር ዘመናዊ ቴክኖሎጂን የታጠቀ ጠንካራ ባህር ሀይል ኢትዮጲያ እንዲኖራት የወጠነው አገሪቱ ትልቅ አገር ስለሆነች ነው" ሲሉ ተናግረዋል። በዚሁ ቃለምልልሳቸው በተጨማሪ "የባህር በር ባይኖረንም ለቀይ ባህርና ህንድ ውቅያኖስ ቅርብ የሆንን አገር ነን። በአሁኑ ወቅት በርካታ አገራት በሱማሊያ፣ ጅቡቲ፣ ፑንትላንድና ኤርትራ የባህር ኃይል ጦር ሰፈር የገነቡበትን ሁኔታ እያየን ነው። ከዚህ አኳያ እኛ ከጠረፍ 60 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ተቀምጠን የራሳችንን ባህር ኃይል ማስፈር እንችላለን" ብለዋል።

ኢትዮጲያ በቀይ ባህር ወደቦች በመጠቀም የወጪና ገቢ ንግድ እስካከናወነች ድረስ ባህር ኃይል ማቋቋም እንደማይከብዳት የተናገሩት ፊልድ ማርሻሉ በቀይ ባህር አካባቢ በርካታ አገራት የባህር ኃይል ጦር ሰፈር እየገነቡ መሆኑን አስረድተውም ካለው ሁኔታ አንፃር፤ "እያድርገውና ቀጣናዊ ቀውስ ቢፈጠር ባህር ላይ ምንም ጉልበት ከሌለን እንጎዳለን" ሲሉ የባህር ኃይል ማቋቋም አስፈላጊነትን ገልፀዋል።

## 5.2 በኢትዮጲያ የባህር ኃይል መመስረት ላይ ያሉ አዎንታዊ እና አሉታዊ ምልከታዎች

ከሶስት አስርት ዓመታት በኋላ የኢትዮጲያ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አብይ አህመድ ከመከላከያ ሰራዊት አባላት ጋር በነበራቸው ምክክር የኢትዮጲያን ባህር ላይ የማደራጀት አላማ እንዳላቸው ማሳወቃቸውን ተከትሎ አንዳንድ አሉታዊ አስተያየቶች ሲንሸራሸሩ ነበር።[18] በተለይም የባህረ ኃይሉ ከተቋቋመ በኋላ በየትኛው የባህር በር ላይ ዘብ ሊቆም ነው? የሚሉና ሌሎች ተያያዥ ጥያቄዎችም ይነሳሉ።

ይህ በሀገር ውስጥ ባሉ ግለሰቦችም ይሁን በሌሎች ሀገራት ጭምር የሚነሳው ጥያቄ እንደየጠያቂዎቹ እሳቤ እና እይታ ሊለያይ ቢችልም አሁን ካለው ዓለም-አቀፋዊ፣ አህጉራዊ፣ ቀጠናዊ እና ሃገራዊ ሁኔታዎች ጋር ሲታይ ግን የባህር በር የሌላቸው ሀገራት የባህር ኃይል እንዲመሰርቱ ግድ የሚሆኑባቸው ሁኔታዎች እንዲህ በቀላሉ የሚታዩ አይደሉም። አንዳንድ ግዜ የሚነሱት ጥያቄዎች ከተራው ግለሰብ ብቻ ሳይሆን ካሁን ቀደም ከነበሩት የባህር ኃይል አባላትም ጭምር ነው።

ይህንን አስመልክቶም ሬር አድሚራል ክንዱ ሲናገሩ፤ "የባህር በር የሌላት ሀገር የባህር ኃይል ለምን አስፈለጋት የሚለው ጥያቄ መነሳት ካለበት ለኢትዮጲያ ብቻ ሳይሆን በዓለም-አቀፍ ደረጃ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሆነው ነገር ግን ባህር ኃይል አቋቁመው ያሉትን ሀገራት በምሳሌነት መጥቀሱ አስፈላጊ ነው። ፓራጓይ፣ አዘርባጃን እና ቦሊቪያ ደግሞ እንደ ኢትዮጲያ የባህር በር የሌላቸው ሃገራት ናቸው። ነገር ግን በቂ የባህር ኃይል አላቸው። በተለይም በዚህ ሉዓላዊ ዘመን ላይ በብዙ ሺህ ማይል ከሚርቋቸው ሃገራት ላይ አህጉራትን አቋርጠው በመምጣት የባህር ወደብ ጭምር በመከራየት የባህር ኃይላቸውን አስፍረው ይገኛሉ። ታዲያ ከባህር ከ60 ኪሎ ሜትር ያነሰ ርቀት ላይ ለምትገኘው ኢትዮጲያ የባህር ኃይል መገንባቱ ለምን የሚለውን ጥያቄ ለሚያነሱት ሁሉ ምላሽ መስጠት ባይጠበቅብንም በዋነኝነት ግን ከዓለማችን ቁልፍ ስትራቴጂክ ቦታዎች መካከል አንዱ በሆነው የምስራቅ አፍሪካ የምትገኘው ኢትዮጲያ ጠንካራ የጦር ሰራዊት ገንብታ ልትግኝ ግን የግድ ይላታል እኛም ይህንኑ ግብ ለማሳካት እየሰራን ነው" ብለዋል።

ሌላኛው ጥያቄ ባህር ኃይሉ መሰረቱን በጂቡቲ ወይንስ በኤርትራ በኩል ያደርጋል የሚለው ሌላኛው ጥያቄ ነው። የኢትዮጲያ የባህር ኃይል ከሚታጠቀው የጦር መሳሪያ አንስቶ ዋና መቀመጫ እና ጥቅም ላይ የሚውሉ መርከቦች አይነት ገና ያልተወሰነ እና ያልታወቀ ሲሆን አሁን በተጨባጭ የባህር ሃይሉን ለማቋቋም የአቅም ማሰባሰብና የስልጠና ስራዎች እየተሰሩ እንደሚገኙ ከባህር ኃይል መረጃዎች ያሳያሉ። በአንድ ወቅት የጠቅላይ ሚንስትሩ የብሔራዊ ደህንነት ጉዳዮች አማካሪ የነበሩት አቶ ተስፋሁን ጎበዛይ ለኢትዮ ኤፍ ኤም እንደተናገሩት፤ "ኢትዮጲያ የባህር ሃይሏን ቀይ ባህርና ኤደን ባህረ ሰላጤ ላይ የማቋቋም ፍላጎት አላት" ብለዋል።

---

[17] ኢትዮጵያ የባህር ሀይል ሰራዊቷን ልታዋቅር ነው - ኢዜአ አማርኛ፤ https://www.ena.et/web/amh/w/am_17199

[18] ኢትዮጲያ፡ ያለ ባሕር በር የባሕር ኃይል? -BBC News አማርኛ፤https://www.bbc.com/amharic/44409395

ኢትዮጲያ በነዚህ አካባቢዎች የሚከናወኑ የሃያላን አገራት የኃይል አሰላለፎችን እንደ ባይተዋር የምትመለከተው መሆን የለበትም። የባህር በር የሌላት ሃገር እንዴት የባህር ኃይል ልታቋቁም ትችላለች? ምን አይነት የባህር ኃይል ለማቋቋም ነው የታሰበው? የሚል አስተሳሰብም አለ። የብሔራዊ ደህንነት አማካሪው በምላሻቸው፤ "ኢትዮጲያ ምን አይነት መርከቦችን ትጠቀማለች ከሚለው አንስቶ ማለትም ዲስትሮየር ነው ኬረር ነው ሜትሮ ሀይል ነው ወይስ ቀላል ሀይል ወይንም አጃቢ ሀይል ነው የሚለው ጉዳይ ገና በጥናት ላይ ያለ ነው" ሲሉ መልሰዋል።

በአሉታዊ መንገድ የሚገልጹ እንዳሉ ሁሉ አዎንታዊ አመለካከትም የሚያንጸባርቁ አሉ። ለምሳሌ የቀድሞው የባህር ኃይል አባል በተቃራኒ፣ የቀድሞው የኢትዮጲያ አየር ኃይል አዛዥ ሜጀር ጀኔራል አበበ ተ/ሃይማኖት ጠቅላይ ሚኒስትሩ የባህር ኃይልን ጉዳይ ሲያነሱ በተለያዩ መንገዶች ሊያሳኩት አስበው እንደሆነ ሃሳባቸውን ያጋራሉ። "አንደኛ ኢትዮጲያዊያን (ሲጠይቁት) የነበረውን የባህር መብት ለማስከበር አስበው ሊሆን ይችላል። እኔም በሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የጥናት ፅሁፌ ላይ ኢትዮጲያ የዓለም-አቀፍ ህግን ተጠቅማ የባህር በር ባለቤት የምትሆንበትን መንገድ ጠቁሜያለሁ። ምናልባት በሂደት የዚህ አካል የሚሆን የባህር ኃይል ለማዘጋጀት አስበው ሊሆን ይችላል።" በማለት የሚያብራሩት ጀኔራሉ፤ በሁለተኛ መንገድነት የሚጠቅሱት የአዘርባጃን እና ካዛኪስታንን ተሞክሮ ነው። ሁለቱ ሀገራት የባህር በር የሌላቸው ሀገራት ቢሆኑም በካስፒያን ባህር ላይ የሚንቀሳቀስ ጦር አላቸው። ይሄን ያሳኩት ከጎረቤት ሀገራት ጋር ባላቸው ስምምነት መሰረት ነው። ኢትዮጲያም ተመሳሳይ ከጂቡቲ ጋር ያላትን መልካም ጉርብትና በመጠቀም የባህር ኃይል ጣቢያ ብሎም የቀይ ባህር ላይ ተሳትፎ ልታደርግ እንደምትችል ያወሳሉ። በኢትዮጲያ መንግስት አስተዳደር ስር በዲፕሎማትነት ያገለገሉት ብርሃነ መስቀል አበበ ሁለተኛው ሀሳብ ሊሳካ የሚችልበትን ዓለም-አቀፋዊ አሰራር ሲያስረዱ፤ "ኢትዮጲያ በዓለም-አቀፍ የውሃ አካላት ላይ አሰሳ ለማድረግ ያላትን መብት ለማሳካት የባህር ኃይል የጦር ሰፈር ይፈልጋል። በቀጠናው የጦር ሰፈር እንዳላቸው ሃገራት ሁሉ በተመሳሳይ ኢትዮጲያም ከጎረቤት ሃገር በአንዱ የባህር ጦሯን ልታሰፍር ትችላለች። የተሳሰሩ ህዝቦች አሉን" ይላሉ።

ወደ ሶስተኛው የሜ/ጀኔራል አበበ ስንመለስ ሶስተኛውን የቦሊቪያን መንገድ ያጋሩናል። "የባህር በር የሌለው ቦሊቪያ የሚባል ሃገር አለ። ከጊዜያት ወዲህ የባህር በሩን ያጣ ሀገር ነው። ይሁንና አሁንም የባህር ኃይል አላቸው። የባህር ሃይላቸውን የሚጠቀሙበት ያጣነው ነገር የለም የሚለውን መንፈስ ለማሳየት እንደ (ሀገራዊ ክብር ማሳያ) ምልክትነት ነው።" ይህ ደግሞ በእርግጥ እስከመቼ ጎረቤት ታምኖ የሚለው ሌላኛው ጥያቄ ያስነሳል።

ሌላኛው የሃሳብ መነሻ "ኢትዮጲያ የባህር በር የማግኘት መብት አላት" በሚል የሚሟገቱት ዶ/ር ያቆብ ሃ/ማሪያምን የ"አሰብ የማናት? የኢትዮጲያ የባህር በር ጥያቄ" መጽሀፍ ደራሲ ሲሆኑ፤ ዶ/ር ያቆብ የጠቅላይ ሚኒስትር አብይ ንግግር በበጎ እንደሚያዩት፣ ሆኖም የባህር በር በሌለበት ሁኔታ የሚሰምርበት ሁኔታ ላይ ጥርጣሬ እንዳላቸው ይገልጻሉ። የጎረቤት ሀገራትን ተማምኖ ጦር ማደራጀትም ያልተፈለገ ውጤት እንዳለው ያነሳሉ። "የጎረቤት ሀገራት ፍቅር እኮ ዘላለማዊ አይደለም። አንዳንዴ በመሃል ጥል፣ ግጭት ይኖራል። ይሄም የበለጠ ኢትዮጲያ በቋፍ ላይ እንድትሆን ያደርጋታል፣" በማለት አስተማማኝ መፍትሄ የሚገኘው ኢትዮጲያ የባህር በር መብቷን ስታረጋግጥ እንደሆነ ዳግም ያሰምራሉ። በተጨማሪም የባህር በር ከሌለ ባህር ኃይል ማቋቋም ቀልድ ነው? የሚሉት ደግሞ የቀድሞ የኢትዮጲያ የባህር ኃይል አባል ናቸው። "ሚሳኤል አስወንጫፊ ጦር መርከቦች ነበሩን። ትልቅ ባህር ኃይል ነው የነበረን። ከባድ የባህር ኃይል ለማቋቋም የግድ የባህር በር ያስፈልጋል፤ የባህር ኃይሉም መፍረስ አልነበረበትም! የኢትዮጲያ ባህር ኃይል ከዓለም ስመ-ጥር ባህር ኃይሎች አንዱ ነበር እስከ ትልቁ የጦር ሚሳኤል ድረስ ታጥቆ ይንቀሳቀስ ነበር። ባህር ኃይል ለኢትዮጲያ አስፈላጊነቱ ወቅቱ እንደውም አልፏል። መፍረስም አልነበረበትም። የባህር በሯ ከተመለሰ ነው ታዲያ ባህር ሳይኖር ኢትዮጲያ የባህር ኃይል አላት ብሎ ማወጅ ፌዝ ነው። የግድ የባህር በር መኖሩ መረጋገጥ አለበት።"[19] ሲሉ ይናገራሉ።

ሀገሪቱ አሁን ባላት የኢኮኖሚ አቅም እንዴት ባህር ኃይል ልታዋቅር ትችላለች የሚለው ደግሞ ከሃገሪቱ የኢኮኖሚ አቅም ጋር አያይዘው የሚሞግቱ ናቸው። "ያደጉ አገራት ሳይቀሩ የኢትዮጲያ ባህር ኃይል ለማቋቋም ትልቅ እርዳታ ያደርጋሉ። ኢኮኖሚዋም ይፈቅዳል የሚረዱንም አገሮች ይኖራሉ።" የሚሉም አይጠፉም። አንዳንዶቹ በተጨማሪ ባህር ኃይልን ሌላ ሃገር መመስረት ወታደራዊ ሚስጥርን ከመጠበቅ አንጻር ጥያቄ የሚያስነሳ መሆኑን ይናገራሉ። የራስ ወደብ ሊኖር የሚችልበት መንገድ ቢቀየስ የባህር ኃይል በመዋቀሩ የሚስማሙም አሉ።

## 5.3 በኢትዮጲያ የባህር ኃይል መኖሩ የሚኖረው እንድምታ እና ፋይዳ

በኢትዮጲያ የባህር ኃይል መኖሩ ብዙ ፋይዳዎች አሉት። ከነዚህም ውስጥ በዋነኝነት የሚጠቀሱት እና ይህ ጥናት ሊመልሳቸው የቻሉት ዋና ዋና ጉዳዮች ከዚህ በታች በዝርዝር ቀርበዋል።

[19] የባህር በር ከሌለ ባህር ሀይል ማቋቋም ቀልድ ነው። DW 29.11.2018፤ https://www.dw.com/am/የባህር-በር-ከሌለ-ባህር-ሀይል-ማቋቋም-ቀልድ-ነው/a-46494464

### 5.3.1 የባህር ላይ ውንብድናን መከላከል

በአሁኑ ጊዜ ዓለም አቀፍ የባህር ላይ ውንብድና የሚፈፀምባቸው ዋነኛዎቹ አካባቢዎች ምዕራብ አፍሪካን የሚያዋስነው የውሃ ክልል (በአትላንቲክ ውቅያኖስ የአፍሪካ ዳርቻዎች) ፣ በኢንዶኔዥያ ዙሪያ የሚገኙ የባህር አካባቢዎች እና የሶማሊያ የባህር ዳርቻዎች ናቸው። በተለይ በሶማሊያው ጠረፍ የሚካሄደው የባህር ላይ ውንብድና እስካሁን ድረስ መፍትሄ አልተገኘለትም። ከአውሮፓ ጋር ከሚደረገው ዓለም-አቀፍ ንግድ 80 በመቶው በኤደን ባህረ ሠላጤ በኩል የሚያልፍ ነው። በአካባቢው የባህር ላይ ውንብድናን ለመከላከል የዓለም ዓቀፋ ማህበረሰብ ባህር ኃይል ከተሰማራበት ከዛሬ 5 አመት ወዲህ ዘረፋና እገታው በእጅጉ ቢቀንስም ሙሉ ለሙሉ ግን ስጋቱና እንቅስቃሴው አልጠፋም። በርሊን የሚገኘው የምጣኔ ሃብት ምርምር ተቋም በባህር ላይ ወንበዴዎች የሚዘረፈውና የታገቱ ሰዎችን ለማስለቀቅ የሚሰጠውን ገንዘብ በአመት ከ7 እስከ 12 ቢሊዮን ዮሮ እንደሚደርስ አስልቷል።

ከባህር ላይ ውንብድና ለመሸሽ የባህሩን መንገድ መቀየር መፍትሄ አይሆንም። መርከቦች ስዌዝ ካናልን ትተው በ17ተኛው ክፍለ ዘመን እንደሚደረገው መላ አፍሪካን በመዞር ጉዞው በ2 ወራት ሊዘገይ ከመቻሉም በላይ ተጨማሪ 30 ቢሊዮን ዩሮ ያስወጣል። ዓለም-አቀፍ የባህር ትራንስፖርት አገልግሎት እ.ኤ.አ. ከ2005 እስከ 2008 ስለተካሄደው የባህር ላይ ውንብድና ባቀረበው ዘገባ በመቶዎች ይቆጠር የነበረው የዘራፊዎች ቁጥር ከአንድ ሺህ በላይ ማደጉን አስታውቋል። በ2005 ፣300 ያህል ጥቃት መድረሱንም አስታውሷል። በዚህም ከ2008 ወዲህ የዓለም-አቀፋ ማህበረሰብ የባህር ኃይል ዝርፊያና እገታ ይካሄድባቸው በነበሩ አካባቢዎች ሰፍሯል።

አታላንታ በተሰኘው የአውሮፓ ህብረት ተልዕኮ ሥር የዘመቱት የጀርመን ባህር ኃይል መርከቦችም የንግድ መርከቦችን ከጥቃት እየጠበቁ ነው። ከዚያን ጊዜ አንስቶም የሚጠለፉና የሚጠቁ መርከቦች ቁጥር ቀንሷል። በነዚህ እርምጃዎች ምክንያት በኤደን ባህረ ሰላጤ የባህር ላይ ውንብድና በአንፃራዊ መቀነሱና አሁን ላይ ዘረፋው ከጥቂት ወራት ወዲህ ወደ ሌላ አካባቢ ተሸጋግሯል ይላሉ በዙሪያው ጥናት የሚያደርጉ ተመራማሪዎች። እነዚህንና ሌሎችንም ምሳሌዎች መሰረት በማድረግ የኢትዮጲያ የባህር ኃይል መቋቋም ለኢትዮጲያ 11 የንግድ መርከቦች ከዚያም ሲያልፍ ለሶማሊያና ለሌሎች ሃገራት ጭምር ዋስትና ሊሆን ይችላል።

### 5.3.2 በአፍሪካ ቀንድ የሚካሄደውን የኃይል አሰላለፍ መቆጣጠር

በአፍሪካ ቀንድ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተበራከተ የመጣውን የጦር ሰፈር እሽቅድድም በጥንቃቄ ለመመልከትና ለወደፊት ሊያመጣ የሚችለውን የደህንነት ስጋት ለመቀልበስ የባህር ኃይል መቋቋሙ ትልቅ ፋይዳ አለው። ሃያላን የሚፎካከሩበት የአፍሪካ ቀንድ አገራት ትብብር የት ድረስ ይዘልቃል? የሚለው ጥያቄ ቀጠናውን የሚከታተሉ የብዙ ተንታኞች ጥያቄ ነው። ኢትዮጲያ፣ ኤርትራ፣ ጂቡቲ፣ ሱዳን፣ ደቡብ ሱዳን እና ሶማሊያን ያካተተው የአፍሪካ ቀንድ አካባቢ በአህጉሪቱ ውስጥ እንዲሁም በዓለም ምጣኔ ሃብታዊ እና ፖለቲካዊ ሁኔታ ውስጥ ወሳኝ ሚና ያለው ስፍራ ነው።

የአፍሪካ ቀንድ ከመካከለኛው ምሥራቅ እና ከባሕረ ሰላጤው አገራት ነዳጅ እና ከእስያ ደግሞ ወሳኝ የኢንዱስትሪ ምርቶች ሰፊ ተጠቃሚ ወዳለባቸው የአውሮፓ እንዲሁም የአሜሪካ አህጉር የሚተላለፍበት ቁልፍ የቀይ ባሕር መተላለፊያ ያለበት ስፍራ ነው። በዚህም የተነሳ ባለፋት ዘመናት እና በአሁኑ ወቅት ኃያላን አገራት በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ካሉ አገራት ጋር ወዳጅነትን በመመስረት ተጽእኖቻቸውን እና ቁጥጥራቸውን ማጠናከር ይፈልጋሉ። በዚህም የተነሳ አካባቢው የኃያላን እና ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ የሚፈልጉ አገራት የመፈንጫ ሜዳ ሆኖ ቆይቷል።[20]

የቀጣናዉን እንቅስቃሴ በአንክሮ ለሚከታተል ሰዉ በእርግጥም እነ ሳዑዲ ዓረቢያ፣ የተባባሩት አረብ ኤመሬትስ እና ቱርክንም ጨምሮ በቀይ ባህር አካባቢ የየራሳቸዉን ጦር ሰፈር ለመገንባት ዋረቶችን ሲያደርጉ ይስተዋላል።በእርግጥ ከቀይ ባህር ሃገራት በተለይም ከአፍሪካ ቀንድ ሃገራት መካከል ጅቡቲን ብንወስድ ሃያላን ሃገራት የጦር ሰፈር ገንብተዉ ከፍተኛ ፉክክር የሚያደርጉባት ሃገር መሆን ከጀመረች ሰነባብታለች።

ቻይና፣ ፈረንሳይ፣ ጣሊያን፣ ጃፓን እና አሜሪካ በጅቡቲ የየራሳቸዉን የጦር ሰፈሮች ገንብተዉ የአፍሪካን የተፈጥሮ ሃብት በኢንቨስትመንት ስም ወይም የየራሳቸዉን ጥቅም ለማስጠበቅ በሚል ሽፋን ጤናማ ያልሆነዉን ፉክክራቸዉን በማጧጧፍ ላይ ናቸዉ። ታዲያ ይህን የተመለከቱ እነ ሳዑዲ ዓረቢያ፣ ኢመሬትስ፣ ኳታርና ቱርክም የየራሳቸዉን ጦር ሰፈር በጅቡቲ ወይም የባህር በር ባላቸዉ የአፍሪካ ቀንድ ሃገራት አካባቢ (ኤርትራ፣ ሱማሊያ፣ ሱማሊ ላንድና ፑንት ላንድ) አካባቢ ለመገንባት የሚያስችላቸውን ስምምነት በመፈራረም የራሳቸውን ቤዝ አቋቁመዋል።[21] ቀስ በቀስም ከዚህ በፊት እንቅስቃሴያቸዉ

---

[20] [ኃያላን የሚፎካከሩበት የአፍሪካ ቀንድ አገራት ትብብር የት ድረስ ይዘልቃል? - BBC News አማርኛ](https://www.bbc.com/amharic/articles/c3grnywjneko)፤ https://www.bbc.com/amharic/articles/c3grnywjneko

[21] Dawit Fantu (2020), the Military Bases of Saudi Arabia and United Arab Emirates in the Horn of Africa and Implications for Ethiopia Foreign Policy

እምብዛም በይፋ ሲንቀሳቀሱ የማይታዩ እንደነ እስራኤልና ህንድ ያሉ ሃገራትም ተመሳሳይ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ መስተዋሉ ነዉ።

ከአሜሪካ ጋር የቆየ ታሪካዊ እና ስትራቴጂካዊ ፉክክር በማድረግ የምትታወቀዉ ሩስያም ብትሆን በቀጣናዉ የምታደርገዉ እንቅሰቃሴ ተፅእኖ ፈጣሪ እንደሆነ ለማስተዋል ብዙ ጉልበት አይጠይቅም። ሩስያ ለአፍሪካ ቀንድ ሃገራት የምታደርጋቸዉ ወታደራዊ ድጋፎች በጣም ከፍተኛ ናቸዉ። በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ያሉ ሃገራት ፀረ አሜሪካ አቋም ይኖራቸዉ ዘንድ የሩስያ ምኞትና ፍላጎት ብቻ ሳይሆን ሩስያ ጊዜዋንም ጉልበቷንም ገንዘቧንም ሳትሰስት የምትዋደቅለት ዓላማዋ ነዉ።

አንድ በ2018 የወጣ ሪፖርት እንደሚያሳየዉ ከሆነ ደግሞ ሃያላን ሃገራት፤ የገልፍ ዐረብ ሃገራትንና ሌሎች የኤስያ ሐሃራትን ማለትም ቱርክን ሩስያንና ህንድን ጨምሮ በቀይ ባህር አካባቢ የሚያደርጉት ፉክክር ጤናማ እንዳልሆነ አረጋግጦ የሰራዉ በኢትዮጲያ፣ ኤርትራ፣ ጅቡቲ፣ ሱማሊያ፣ ሱማሌላንድ፣ ሱዳን፣ የተባበሩት አረብ ኤመሬትስ፣ ሳዑዲ-ዓረቢያ፣ ኳታር፣ ቱርክ፣ አሜሪካ የሚገኙ ምሁራንን እና ፖለቲከኞችን አነጋገሮ እንደሰራዉ ይፋ አድርጓል።[22] ከገልፍ ሃገራት መካከል በአፍሪካ ቀንድ ፖለቲካ ረጅም እጅ እንዳላት የሚመሰክርላትና በቀጣናዉ ጉልህ ሚና አላት የሚባልላት አረብ ኤመሬትስ በቀጣናዉ እዚህም እዛም እየታየች ነዉ። አረብ ኤመሬትስ እና ሳኡዲ አረቢያን ወደ ቀጣናዉ የገፋፏቸው ሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች አሉ እነሱም አንደኛዉ በ2015 በየመን የተቀሰቀሰው ጦርነትና የእርሷ ዋና ተዋናይነት ሲሆን ሁለተኛዉ ደግሞ በቱርክ ታግዛ በቀጣናዉ ሌላ ፉክክር በማድረግ ላይ የምትገኘዉን ኳታርን ለመቀናቀን ብሎም የእነ ቱርክን እንቅስቃሴ ሙሉ ለሙሉ ለማስቀም ነዉ።[23] እዚህ ላይ አንድ ልብ ልንለዉ የሚገባ ነገር አለ እሱም ኢመሬትስና ሳዑዲ ዓረቢያ ፀረ ቱርክ አቋም ይዘዉ የእነ ኳታርንና የእነ ቱርክን እንቅስቃሴ ለማስቆም ተናበዉ እና ተደጋግፈዉ የሚሰሩ የአንድ ሳንቲም ግልባጮች መሆናቸዉን ነዉ።[24] ከዚሁ ሃሳብ ሳንወጣ በአንድ ወቅት የኢ.ፌ.ድ.ሪ. የጦር ሃይሎች ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ማርሻል ብርሃኑ ጁላ እንደተናገሩት "የባህር በር ባይኖረንም ያለንበትን ቀጠና ከግምት በማስገባት የራሳችንን የባህር ኃይል በቀይ ባህር ላይ ማስፈር አለብን።" ይህ ሁሉ በአፍሪካ ቀንድ ያለው ትርምስና የጦር ሰፈር ቅርምት ነገ ምን ይዞ እንደሚመጣ አይታወቅም።

### 5.3.3 የውስጥ እና ድንበር ተሻጋሪ ውሃማ አካላትን ደህንነት ማስጠበቅ

አገራችን ኢትዮጲያ በሉዓላዊ የግዛት ወሰኗ ውስጥ ትላልቅ ሰው ሰራሽ እና የተፈጥሮ ውሃማ አካላቶች (ሃይቆች) አሏት። እነዚህም ውሃማ አካላት በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ ሲሆን እንደየ ጂኦግራፊያዊ አቀማመጣቸው ለባህር ኃይል የሚኖራቸው ግዳጅ የተለያየ ይሆናል። በኢትዮጲያ የህዳሴው ግድብን ጨምሮ በርካታ ድንበር የሚሻገሩ እና የማይሻገሩ ሰው ሰራሽ እና የተፈጥሮ ሃይቆች ይገኛሉ። በስፋታቸው ከህዳሴው ግድብ ቀጥሎ የሚገኙት ዋና ዋናዎቹ ናቸው። ጣና ሐይቅ (3,000 ስኩዌር ኪ.ሜ)፣ አባያ ሀይቅ (1,162 ስኩዌር ኪ.ሜ)፣ ጫሞ ሐይቅ (551 ስኩዌር ኪ.ሜ)፣ ዝዋይ ሐይቅ (440 ስኩዌር ኪ.ሜ)፣ አቤ ሐይቅ (336 ስኩዌር ኪ.ሜ)፣ ሻላ ሐይቅ (329 ስኩዌር ኪ.ሜ)፣ ላንጋኖ ሐይቅ (230 ስኩዌር ኪ.ሜ)፣ አቢያታ ሐይቅ (205 ስኩዌር ኪ.ሜ)፣ የቆቃ ግድብ ሀይቅ (180 ስኩዌር ኪሎ ሜትር)፣ ሀዋሳ ሐይቅ (129 ስኩዌር ኪሎ ሜትር) ናቸው።

ድንበር ተሻጋሪ ውሃዎች በሁለት ወይንም ከዛ በላይ በሆኑ አገሮች መካከል የሚገኙ ናቸው። እነዚህ ውሃማ አካላት ተገቢ የሆነ የድንበር ውሃዎች ቁጥጥር ካልተደረገባቸው ለህገወጥ እንቅስቃሴ ምቹ የመሆን እድላቸው እጅግ ሰፊ ነው። በሃገራችን ሁለት ትላልቅ ድንበር ተሻጋሪ ሃይቆች ይገኛሉ። እነዚህ ሃይቆች ለዚህ ጥናት አለማ በተደረገው የመረጃ ማሰባሰብ ሂደት በርከት ያሉ መላሾች ጥያቄ ቀርቦላቸው እንደማያውቋቸው ገልፀዋል። ጥቂቶች ደግሞ በኬኒያ የሚገኙ ናቸው የሚል የጥርጣሬ መልስ ሰጥተዋል። እነዚህም ሃይቆች ቱርካና ወይም ሩዶልፍ፣ አቤ ሃይቅ እና ጨው ባህር ሃይቅ ናቸው። ቱርካና ሃይቅ በኢትዮጲያ እና ኬኒያ መካከል የሚገኝ ሃይቅ ሲሆን ከሰሜን ወደ ደቡብ ሲለካ እስከ 250 ኪሎ ሜትር የሚደርስ ርዝመት አለው። ከዚህ ጠቅላላ ርዝመት ውስጥ ወደ 20 ኪሎ ሜትር የሚጠጋው ክፍሉ በኢትዮጲያ የግዛት ወሰን ውስጥ የሚገኝ ነው። የሃይቁ የጎን ስፋት በአማካኝ እስከ 30 ኪሎ ሜትር ይደርሳል።

በቅርቡ ከኡጋንዳ ምስራቃዊ ክፍል ከምትገኘው ሰሬሬ ወረዳ መነሻቸውን ያደረጉ 100 የሚሆኑ የክራይስ ዲሲፕልስ ቸርች የተባለ እምነት ተከታዮች በአንድ ወገን የምፅዐት ቀንን ለመሸሽ በሌላ ወገን ደግሞ የቤተ ክርስቲያን መልዕክት ለማድረስ በሚል በቱርካና ሃይቅ በኩል በማድረግ በርካታ መቶ ኪሎ ሜትሮችን በማቋረጥ በደቡብ ኦሞ ዞን በኛንጋቶም ወረዳ መገኘታቸው በድንበር ተሻጋሪ ውሃዎች ሊከሰቱ የሚችሉ ህገ-ወጥ እንቅስቃሴዎች ማሳያ ነው። በተመሳሳይ በዚሁ ሃይቅ ላይ ሰፊ የሆነ

---

[22] US Foreign Affairs megazin, 2019

[23] Dawit Fantu

[24] [አዲሱ የቀይ ባህር ጂኦ ፖለቲክስ እና የሓያላን ሐገራት ፉክክር – ክፍል 1 – Awash FM]፤ https://awashfm.com/%E1%8A%A0%E1%8B%B2%E1%88%B1

ህገ-ወጥ አሳ ማስገር እንዲሁም ወደ ጎረቤት አገር ሰፊ የጭነት አገልግሎት የሚሰጡ ጀልባዎች እንዳሉ በአካባቢው በተለያዩ ጊዜያት ይሰሩ የነበሩ ነዋሪዎች ይነገራል።

በሁለተኛነት የሚገለፀው አቤ ሃይቅ በኢትዮጲያ እና ጂቡቲ መካከል የሚገኝ ጨዋማ ሃይቅ ነው። ሃይቁም ከምስራቅ ወደ ምዕራብ ያለው ስፋቱ ከ15 ኪሎ ሜትር በላይ የሚገመት ሲሆን ከሰሜን ወደ ደቡብ ያለው ስፋቱ ደግሞ ከ10 ኪሎ ሜትር በላይ ነው። ይህ ሃይቅ አብዛኛው ክፍሉ በኢትዮጲያ የግዛት ወሰን ውስጥ የሚገኝ ነው። ይህም እስከ 10 ኪሎ ሜትር ይደርሳል።

ሶስተኛው ድንበር ተሻጋሪ ሃይቅ ጨው ባህር ሃይቅ ይባላል። በደቡብ ኦሞ ዞን አካባቢ ከቱርካና ሃይቅ በስተምዕራብ በ70 ኪሎ ሜትር ርቀት ውስጥ የሚገኝ ሃይቅ ነው። ይህ ሃይቅ አብዛኛው ክፍሉ በኢትዮጲያ የግዛት ወሰን ውስጥ የሚገኝ ሲሆን እስከ 4 ኪሎ ሜትር ድረስ ሊዘልቅ የሚችል ክፍሉ በሰሜን ኬኒያ ድንበር ውስጥ ይገኛል።

### 5.3.4 **የትላልቅ ፕሮጀክቶችን ደህንነት ማረጋገጥ**

በአገራችን ኢትዮጲያ በርካታ ለኤሌክትሪክ ማመንጫ እና ለመጠጥ ውሃ አገልግሎት የሚውሉ እንደ ፊንጫ፣ ግልገል ጊቤ፣ ኮይሻ፣ መልካ ዋከና፣ ጣና በለስ፣ ተከዜ፣ ታላቁ የህዳሴ ግድብ እና ገናሌ ዳዋ የመሳሰሉት ግድቦች ይገኛሉ። እነዚህ ከፈሰሰባቸው መዋዕለ ንዋይ እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች በመነሳት ልዩ የሆነ ጥበቃ ያስፈልጋቸዋል።

***የግድቦችን ፊዚካል ደህንነት መጠበቅ***

በአገራችን ቀላል የማይባሉ ትላልቅ ሰው ሰራሽ የኤሌክትሪክ ማመንጫ እና የመጠጥ ውሃ ግድቦች አሉ። እነዚህ ግድቦች ልዩ ጥበቃ ይፈልጋሉ። ለምሳሌ ታላቁን የህዳሴ ግድብ ብንመለከት የግድቡ መገኛ ለድንበር እጅጉን የቀረበ በመሆኑ ማለትም ዋናው የኃይል ማመንጫ ከሱዳን ድንበር በ20 ኪሎ ሜትር ርቀት እንዲሁም የኮርቻ ግድቡ በተመሳሳይ ከድንበር ከ5-7 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ስለሚገኝ ድንበር ተሻግረው ለሚመጡ ስጋቶችም የተጋለጠ በመሆኑ ተገቢ የሆነ የውሃ ላይ፣ ከውሃ ወደ መሬት እና ከመሬት ወደ ውሃ ጥበቃ ይፈልጋል። ግድቦች የኃይል ማመንጫ ፓወር ሃውሳቸው የክልክል ወረዳ (Buffer Zone) ተበጅቶላቸው ከማንኛውም አይነት እንቅስቃሴ ነፃ መሆን ይገባቸዋል። ይህ ስራ ደግሞ አንዳንድ ግደቦች ከሃይቆቻቸው ስፋት በመነሳት በውሃ ላይ በጀልባ እንቅስቃሴ በማድረግ ጭምር የሚከናወን መሆን አለበት።

***በተፈቀደው የውሃ አካላት ወሰን ውስጥ ያሉ ተግባራትን መቆጣጠር፡-***

የህዳሴ ግድብን ጨምሮ ትላልቅ የኃይል ማመንጫዎቻችን ከኃይል ማመንጨት ባሻገር በሃይቆቻቸው ላይ የተለያዩ እንቅስቃሴዎች ይኖራሉ። እነዚህም እንቅስቃሴዎች የተለያዩ ስጋቶች ምንጭ ሊሆኑ ስለሚችሉ ከወዲሁ ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል። በትላልቅ የኃይል ማመንጫዎች ላይ የውሃ ትራንስፖርት፣ የአሳ ማስገር እና የቱሪስት እንቅስቃሴዎችን ማድረግ የተለመደ ነው። ይህ ሲሆን ግን የግድቦችን ዋና ተልዕኮ በማያስተጓጉል መልኩ እንቅስቃሴው በሙሉ ፊጉሌት መደረግ አለበት። በዚህም መሰረት፡-

- በሃይቆች ላይ የሚደረግ የውሃ ላይ ትራንስፖርት በመሬት ላይ ከሚደረገው የትራንስፖርት ቁጥጥር በመነሳት የራሱ የሆነ ፕላትፎርም ይፈልጋል። ለምሳሌ በህዳሴው ግድብ አካባቢ በየብስ የትራንስፖርት አማራጭ ሲደረጉ የነበሩ የረጅም ሰዐት ጉዞዎች በሙሉ በአጭር ሰዐት የውሃ ላይ ጉዞ ስለሚተኩ በመሬት ላይ የነበሩት ስጋቶች በሙሉ ወደ ህዳሴ ሃይቅ ይሸጋገራሉ ማለት ነው።

- ድንበር ተሻጋሪም ይሁን የውስጥ መዳረሻ ያላቸውን ሕገወጥ የአሳ ማስገር እንቅስቃሴዎች በመግታት የአገርን ኢኮኖሚ መደገፍ ያስፈልጋል። የህዳሴውን ግድብ በምሳሌነት ብንወስድ ሰው ሰራሽ ሃይቁ ሰፊ የሆነ የአሳ ልማት ቦታ መሆኑ አይቀሬ በመሆኑ፣ በሃይቁ ዙሪያ ዘመናዊ የአሳ ልማት እንዲሁም በዙሪያው ትናንሽ ባህላዊ የአሳ ማስገር ተግባራቶች በህጋዊም ይሁን ህገወጥ መንገድ ሊከናወኑ ስለሚችሉ የተጀመሩም ስላሉ ከመሰረቱ የህግ ማዕቀፍ እንዲኖረው ማድረግ ያስፈልጋል። ካልሆነ ግን ድንበር ዘለል ህገውጥ እንቅስቃሴዎች መፈጠራቸው የማይቀር ነው።

- ለአጭር ጊዜ ወይንም አዳርን ጨምሮ ለረጅም ጊዜ በሃይቆች አካባቢ የውጭ ቱሪስቶችን ጨምሮ ወደ ትላልቅ ፕሮጀክቶች ፍሰቱ ከፍተኛ መሆኑ አይቀርም። በዚህም ምክንያት ፕሮጀክቶች ስጋት ውስጥ ሊወድቁ ይችላሉ። በመሆኑም ወደ ግድቦች በተለይ እንደ ህዳሴ ግድብ ያሉትን ተርሚናል በማበጀት ወጥ በሆነ የደህንነት ማረጋገጫ ብቻ አልፈው እንዲስተናገዱ ማድረግ ያስፈልጋል። በተለይ የህዳሴ ግድብ በሰው ሰራሽ ሃይቅ ላይ በሚገኙት ደሴቶች ላይ የተለያዩ የቱሪስት መስህብ የሚሆኑ መሰረተ ልማቶች የሚመሰረቱ በመሆኑ በርከት ያለ የቱሪስት ፍሰት ከቅርብም ከሩቅም የሚመጣ በመሆኑ ከፍተኛ ጥንቃቄ ያለው የደህንነት መቆጣጠሪያ ሲስተም ሊኖረው ይገባል።

***የውሃ ላይ ነፍስ ማዳን ስራዎች***

የሃይድሮ ኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ግድቦች ግድቡ ይዘውት የሚመጡት ተስፋ በርካታ የሰው እንቅስቃሴ ስለሚያመጣ በዛው ልክ አደጋዎች ሊፈጠሩ ስለሚችሉ የነፍስ ማዳን ስራዎች ስለሚኖሩ በየትኛውም ሁኔታ ውስጥ አስቸኳይ የነፍስ ማዳን ስራ የሚሰራ የሰለጠነ እና የታጠቀ የሰው ኃይል በአጭር ጊዜ ተንቀሳቅሶ ግዳጅን መወጣት የሚችል ኃይል መገንባት ተገቢ ነው።

**6. በጎረቤት ሃገር እና በቀጠናው ከሚገኙ ባህር ኃይሎች ጋር ሊኖር የሚገባው የስራ ግንኙነት**

የባህር በር የሌላቸው ሃገራት የንግድ መርከቦቻቸውን ደህንነት ለመጠበቅ፤ ለሁሉም ክፍት የሆነውን ዓለም-አቀፍ የባህር እና የውቅያኖስ አካል ለመጠቀም፤ ሽብርተኝነትና እና የባህር ላይ ውንብድናን ለመከላከል መሳተፍ እንዳለባቸው ተዘርዝሯል። በተጨማሪም ሃገራት ድንበር ተሻጋሪ የሆኑ የታላላቅ ሃይቆች እና የወንዝ ድንበሮቻቸውን ለማስጠበቅ ከዚህም ባለፈ እነዚህ ሃገራት ይህንን የጋራ የውሃ ሃብት በፍትሃዊነት ለመጠቀምና ደህንነቱን ለመጠበቅ ይረዳ ዘንድ ባህር ኃይል ያቋቋሙበት ሁኔታ አለ።

ወደ ሃገራችን ስንመለስ በቀጠናው ላይ የሚኖረው የውጪ ወታደራዊ ሃይሎች የመብዛት ሁኔታ የራሱ የሆነ ጠቀሜታ እና በዛው ልክ በርካታ ስጋቶችን ይዞ የሚመጣበትም እድል አለው። የወታደራዊ ሃይሎች አሰላለፍ ይዞት የሚመጣው ስጋት እና ተስፋ በአራት ዋና ዋና ዘርፎች ይመደባሉ። እነሱም በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ እና በፀጥታ መስክ እንደሚታዩ የተለያዩ ምንጮች ያስረዳሉ። በዚህ ረገድ ኢትዮጲያ እንዴት ከጎረቤትና በዙሪያ ወይም በቀጠናው ወታደራዊ ሰፈር መስርተው ከሚንቀሳቀሱ ሃገራት እና ከጎረቤትና በአካባቢው ካሉ የባህር ኃይል ጋር እንዴትና በምን ላይ ትስራ ምን አይነት ግንኙነት ይኑራት የሚለው ሃሳብ ዋነኛውና ጥንቃቄ መደረግ ያለበት ነገር ነው።

- በቀጠናው ያሉ የጋራ የሆኑ ተልዕኮዎችን በተመለከተ ወቅታዊ እና በቴክኖሎጂ ተደግፈው የተሰበሰቡ የመረጃ ልውውጥ ማድረግ ዋነኛ ስራ መሆን አለበት ተብሎ ይታመናል። ለምሳሌ የባህር ላይ ውንብድና፤ ህገወጥ የሰዎች ዝውውር እና የጦር መሳሪያ ሽያጭ መረጃ መቀያየር፤

- በቀጠናው ላይ እየተስፋፋ ያለው ኃይል በአብዛኛው የባህር ኃይል በመሆኑ ለቀጠናው ሃገራት የባህር ኃይላቸውን በማሳደግ በኩል ከፍተኛ ድጋፍ ያደርጋል። እንዲሁም የምድር እና አየር ሃይሎች ጋር የተሻለ ወታደራዊ ትብብር ለመፍጠር እና የልምድ ልውውጥ በማድረግ ዘመቻዎችን በጋራ መወጣት እና ክህሎትን ማደበር ዋነኛው ተግባር መሆን ይኖርበታል።

- በትብብር ለመስራት በሚደረገው ሂደት ውስጥ ኢትዮጲያ ወታደራዊ አቅሞቿን ተጋልጠው እንዳይሰጡ ጥንቃቄና ታክቲካዊ አካሄዶችን በመጠቀም መንቀሳቀስ እና ትብብር መፍጠር፤

- በቀጠናው ላይ ያሉ ወታደራዊ ሃይሎች ከስጋት ነፃ የንግድ መስመርና ቀጠና በመፍጠር እንቅስቃሴውን በማሳለጥ በኩል ኢትዮጲያ ለአንዱ ብቻ ወገንተኛ ከመሆን በራቀ መልኩ እና ታክቲካዊ ሚናዋን መወጣት፤

- ሃያላኑ ለራሳቸው የሚገነቡት መሰረተ ልማት ለሃገራችንም ለቀጠናውም እድገት ጠቀሜታ ስለሚኖረው በጋራ መስራት እና መጠበቅ ላይ ያለመ ተሳትፎ ማድረግ አለባት።

ባጠቃላይ ሃገሪቱ ሉዋላዊነቷንና ብሄራዊ ጥቅሟን ባስጠበቀ እንዲሁም ከሁሉም ሃገራት ጋር በተከባበር መልኩ መንቀሳቀስ ይኖርባታል።

**7. ማጠቃለያ**

ይህ ጥናት ዓይነታዊ ምርምር ሆኖ ዲዛይኑ ደግሞ ገላጭ ምርምር ነው። ለዚህ ጥናት የንሞና አወሳሰዱ የአላማ ተኮር ንሞና ሲሆን ተመራማሪዎቹ ከጥናቱ ጋር ተያያዥነት አላቸው ተብሎ የታመነባቸውን አካላት በቃለ መጠይቁ ተሳታፊ አድርጓል። የባህር ኃይል መቋቋም የባህር ኃይል እና የኢትዮጲያ ብሔራዊ ደህንነት ለኢትዮጲያ ቅንጦት ወይስ የህልውና ጉዳይ በሚል ርዕስ ለተሰራው ምርምር ተያያዥ ሊሆኑ የሚችሉ የባህር ኃይል አባላት፣ ስልጠና ተቋማት አዛዦች ፣ የሰላም እና ደህንነት ጉዳዮች ተንታኞች፤ በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ትንተና በመስጠት የታወቁ ተንታኞች በዚህ ንሞና ውስጥ ተካተዋል። የሚዲያ ገለጻዎች በተመለከተ የባህር ኃይል ከተቋቋመበት/እንዲቋቋም ከተወሰነበት ግዜ አንስቶ ያለውን የ4 አመት የሚድያ አምዶችን ለመዳሰስ ተችሏል። በስተመጨረሻም እነዚህ ከታች የተዘረዘሩት ዋና ዋናዎቹ የጥናቱ ግኝቶች ናቸው።

**በኢትዮጲያ የባህር ኃይል መመስረት ላይ ያሉ አዎንታዊ እና አሉታዊ ምልከታዎች**

የባህር በር የሌላት ሀገር ለምን የባህር ኃይል አስፈለጋት? የሚለውን ጥያቄ በመንተራስ በተለያዩ ግዜያት በኢትዮጲያ የባህር ኃይል መቋቋምን ተከትሎ በተለያዩ አካላት እና ዜጎች የምልከታ ልዩነት፣ የግንዛቤ እጥረት መኖሩ በዳሰሳው ለማወቅ ተችሏል። በተለይም ኢትዮጲያ ሀገራችን አሁን ላይ እያደራጀችውና እየገነባችው ካለው የባህር ኃይል ጋር ተያይዞ በየትኛው የባህር በር ላይ ዘብ ሊቆም ነው? የሚሉና ሌሎች ተያያዥ ሀሳቦችም ይነሳሉ። ይህ በሀገር ውስጥ ባሉ ግለሰቦችም ይሁን በሌሎች ሀገራት ጭምር የሚነሳው ጥያቄ እንደየጠያቂዎቹ እሳቤ እና እይታ ሊለያይ ቢችልም አሁን ካለው ዓለም ዓቀፋዊ፣ አህጉራዊ፣ ቀጠናዊ እና ሃገራዊ ሁኔታዎች ጋር ሲታይ ግን የባህር በር የሌላቸው ሀገራት የባህር ኃይል እንዲመሰርቱ ግድ የሚሆኑባቸው ሁኔታዎች እንዲህ በቀላሉ የሚታዩ አለመሆናቸው በቃለ መጠይቁና በአዎንታዊ መልኩ በሚዲያ ከተዳሰሱ ሃሳቦች ለመረዳ ተችሏል።

**የባህር ኃይል እና የኢትዮጲያ ብሔራዊ ደህንነት**

ኢትዮጲያ ትልቅ ሃገር ናት ! ያለችበት ቀጠና ደግሞ በጣም የተወሳሰበ እና የብዙ ሃያላን ሀገራት እና የባህረ ሰላጤው ሃገራት ጭምር መራኮቻ የሆነበት ነው። እንዳንድ ግዜ ቆም ብለን ራሳችንን መጠየቅ አለብን ለምን እነዚህ ሃገራት በዚህ አካባቢ የጦር ሰፈር ማቋቋም አስፈለጋቸው? ምንስ አስበው ነው? የሚሉት ነገር መፈተሽ አለበት። ሃገሪቱ ብዙ ግዙፍ መርከቦች አሏት ቀጠናው ደግሞ በባህር ላይ ውንብድና የሚስተዋልበት አካባቢ ነው። መርከቦቻችን የተደራጀ ጥበቃ ያስፈልጋቸዋል። በነዚህ እና ሌሎች ምክንያቶች የህልውና ጉዳይ መሆኑ በጥናቱ ለመገንዘብ ተችሏል።

**የባህር ኃይልስ ለምን ይቋቋማል ለምንስ ያስፈልጋል**

ብዙ ሃገራት የባህር ኃይል የሚያቋቁሙት የባህር ክልላቸውን ለማስጠበቅ ሲሆን ከዚህም ሲያልፍ አለማቀፉን የባህር ደህንነት ለመጠበቅ፤ ለትላልቅ የጦር መሳሪያ ሽያጭ ማጓጓዣነት፤ የባህር ላይ ውንብድናን በመከላከል የንግድ መርከቦቻቸውን ደህንነት ለማስጠበቅ፤ በምድር አካል ላይ በመሆን ሊመከቱ የማይችሉ የጠላት ኃይል እንቅስቃሴን ለመመከት፤ በዓለም አቀፉ የባህር ክልል ላይ ለሚደረጉ የተፈጥሮ ሃብት ጥበቃና ልማት ላይ ለመሰማራት፤ የባህር ላይ ህገ ወጥ የሰው ዝውውርና የመሳሪያ ሽያጭን ለመቆጣጠር ታሳቢ እያደረጉ ነው። ከሁሉም በላይ በዓለም አቀፉ መርህ መሰረት ማንኛዉም ሃገር ከዓለም አቀፉ ባህርን የመጠቀም መብት እንዳለው ድንጋጌዎች ተቀምጠዋል ። በተመሳሳይ የባህር በር የሌላቸው ሃገራት የንግድ መርከቦቻቸውን ደህንነት ለመጠበቅ፤ ለሁሉም ክፍት የሆነውን አለማቀፍ የባህር እና የውቅያኖስ አካል ለመጠቀም፤ ሽብረተኝነትና እና የባህር ላይ ውንብድናን ለመከላከል መሳተፍ እንዳለባቸው በተጨማሪም ሃገራት ድንበር ተሻጋሪ የሆኑ ታላላቅ ሃይቆች እና ወንዞች በፍትሃዊነት ለመጠቀምና ደህንነቱን ለመጠበቅ ይረዳ ዘንድ ወደዚህ ወደ ማቋቋም የገቡበት ሁኔታ መኖሩን ጥናቱ አሳይቷል።

**በአፍሪካ ቀንድ ያለው ሽኩቻና የወደብ ግንባታና የጦር ሰፈር ምስረታ እሽቅድድም**

የአፍሪካ ቀንድ በሃያላን ሃገራት እና በባህረ ሰላጤው ሃገራት እይታ ውስጥ በመግባቱ አካባቢው ላይ ለመስፈር እና ተፅዕኖ ለመፍጠር ከፍተኛ ፉክክር እየታየ ነው። ለምሳሌ በጅቡቲ የፈረንሳይ፤ ቻይና እና አሜሪካ የጦር ሰፈር መኖሩ፤ በሶማሌ ላንድ የተለያዩ የባህረ ሰላጤው ሃገራትና ቱርክ በአካባቢው የወደብ ግንባታ ፉላጎት ማሳየታቸው፤ በተጨማሪም እነዚሁ ሃገራት የጦር ሰፈር ማቋቋማቸው ቀጠናው ምን ያህል ሳቢ መሆኑን ያሳያል።

የሃያላን በአፍሪካ ቀንድ የሚያደርጉት የሚሊታራይዜሽን አሽቅድድም ከፀጥታ አንፃር በርካታ ተስፋዎችን ቢያመጣም ቀላል የማይባሉ ስጋቶችም አሉት።

- በትብብር ለመስራት በሚደረገው ሂደት ውስጥ በቀጠናው ያሉ ሃገሮች ወታደራዊ አቅሞቻቸውን በሙሉ አሳልፈው ለሶስተኛ ወገን መረጃ እንዲሰጡ ያደርጋቸዋል። ይህም ለሌላ ጠላት ተላልፎ መረጃ እንዲተላለፍ በር ይከፍታል።
- ለተቃራኒ ሃይሎች ወታደራዊ ድጋፍ በማድረግ ጉዳት ሊያመጡ ይችላሉ።
- ሃገራቱ በራሳቸው አቅም እና ፍላጎት ላይ ተመስርተው መከላከያቸውን እንዳይገነቡ ጫና ሊያደርጉ ይችላሉ።

በቀጠናው ላይ እየተስፋፋ ያለው የወታደራዊ ሃይሎች ካምፕ እና የተለያዩ ዘመቻዎችን ማቋቋም በፖለቲካውና በኢኮኖሚው መስክ ስጋትና ተስፋዎችን ይዞ ሊመጣ ይችላል። በፖሊቲካው እና በኢኮኖሚው መስክ ሊከሰቱ ከሚችሉት ዋና ዋና ስጋቶች መካከል፡-

- በሃያላኑ መካከል በሚደረገው የበላይነትን የማረጋገጥ ሽኩቻ ቀጠናውን የበለጠ ወታደራዊ መናኸሪያ በማድረግ ለህገወጥ የመሳሪያ ዝውውር እና ሽያጭ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል።
- በሃገሮች መካከል ያለውን በንግግር ሊፈቱ የሚችሉ ቅራኔዎች እና አለመግባባቶች የበለጠ የማካረር እድል ይኖረዋል።
- በቀጠናው ላይ ካሉ ሃገሮች ጋር በኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ ኢትዮጲያ በሚኖራት ፍላጎት ላይ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ሃገራቱ ጣልቃ በመግባት የሶስተኛ ወገን ጫና ሊያሳድሩ ይችላሉ።

**በጎረቤት ሃገር እና በቀጠናው ከሚገኙ ባህር ኃይሎች ጋር ሊኖር የሚገባው የስራ ግንኙነት**

ኢትዮጲያ እንዴት ከጎረቤትና በዙሪያ ወይም በቀጠናው ወታደራዊ ሰፈር መስርተው ከሚነቀሳቀሱ ሃገራት እና ከጎረቤትና በአካባቢው ካሉ የባህር ኃይል ጋር እንዴትና በምን ላይ ትስራ ምን አይነት ግንኙነት ይኑራት የሚለው ሃሳብ ዋነኛውና ጥንቃቄ መደረግ ያለበት ነገር መሆኑ ከተለያዩ መላሾች ለመረዳት ተችሏል።

- በቀጠናው ያሉ የጋራ የሆኑ ተልዕኮዎችን በተመለከተ ወቅታዊ እና በቴክኖሎጂ ተደግፈው የተሰበሰቡ የመረጃ ልውውጥ ማድረግ ዋነኛዋ ስራ መሆን አለበት ተብሎ ታምኗል። ለምሳሌ የባህር ላይ ውንብድ፤ ህገወጥ የሰዎች ዝውውር እና የጦር መሳሪያ ሽያጭ መረጃ መቀያየር፤ እና የልምድ ልውውጥ በማድረግ ዘመቻዎችን በጋራ መወጣት እና ክህሎትን ማደበር ዋነኛው ተግባር መሆን ይኖርበታል።

- በትብብር ለመስራት በሚደረገው ሂደት ውስጥ ኢትዮጲያ ወታደራዊ አቅሞቿን ተጋልጠው እንዳይሰጡ ጥንቃቄና ታክቲካዊ አካሄዶችን በመጠቀም መንቀሳቀስ እና ትብብር መፍጠር የሚሉ ሃሳቦች በዳሰሳው ወቅት ለማወቅ ተችሏል።

## 8. የመፍትሔ ሐሳብ

ከላይ በዝርዝር ያየነው በአፍሪካ ቀንድ እና አካባቢው ላይ ያለው የጦር ሰራዊት ክምችት ቀጠናው ያለውን ዓለም አቀፍ ተፈላጊነት እንዲሁም የስጋት ቀጠና መሆኑን ያሳያል። ከዚህ በመነሳት ከላይ ያየነው እውነታ ለኢትዮጲያ ምን ማለት ነው? ቁልፍ ጥያቄ መጠየቅ ተገቢም ግድም ነው። በመነሻ ላይ እንደተገለፀው በጂቡቲ እና በሌሎች ጎረቤት ሃገሮች የአለማችን ሃያላን እና የተወሰኑ አረብ ሃገራት የተለያዩ ተልዕኮችን አንግበው በአካባቢው ይንቀሳቀሳሉ። እንዲሁም ባለ 28 አባል ሃገራቱ የአውሮፓ ህብረት እና ባለ 30 አባል ሃገራቱ የሰሜን አትላንቲክ የጦር ቃል ኪዳን ድርጅት ለአመታት ግዳጆችን እየተወጡ ይገኛሉ። ይህም ሲጠቃለል በዓለማችን ካሉ 200 ከሚጠጉ ሉዓላዊ ሃገሮች ውስጥ አንድ ሶስተኛ የሚሆኑት በቀጠናው ላይ ጉዳይ አለን ብለው ሃብት አፍስሰው መዋያ ማደሪያቸውን እዛ ማድረጋቸው ሊጤን ይገባል።

ከዛም ባሻገር ብሄራዊ ጥቅማችንን ከምንጊዜውም በላይ ለማስጠበቅ ቀጠናው ላይ ባለው የሃያላንና የአረቦች ርብርብና ቅርምት ውስጥ እጃችንን አስገብተን በባለቤትነት አቅማችን በፈቀደው ልክ ልንሳተፍ እና በውሃ ላይ ድፕሎማሲ አወንታዊ ሚና ልንጫዎት ይገባናል ሲሉ ይስተዋላሉ። ኢትዮጲያም በአጠቃላይ በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ እየታየ ያለውን የውሃ ላይ የኃይል አሰላለፍ በፅኑ በመረዳት መነሻቸውን ውሃ ያደረጉ ስጋቶችን መለየት እና ማስቀረት ከተከሰተም መመከት የሚችል ዘመኑን የዋጀ የባህር ኃይል ሊኖራት ግድ ይላል። ባህር ኃይሉም በዋነኝነት ትኩረት እና ቅድሚያ ሰጥቶ ሊያከናውናቸው የሚገቡ ተግባራት እንደሚከተሉት ተዘርዝረዋል።

**የባህር በር አስፈላጊነት ላይ የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራ መስራት**

የተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ለዜጎች በኢትዮጲያ የባህር ኃይል ማቋቋም አስፈላጊ እና የህልውና ጉዳይ መሆኑን ማስተማርና ዜጎች ለዚህ አለማ አበርክቶት የራሳቸውን ሚና እንዲጫወቱ ለማድረግ በመከላከያ ኢንዶክትሪኔሽን በኩል ትልቅ እና ሰፊ ስራ መስራት።

**የሁኔታዎች ጥናትና የመረጃ አቅምን ማሳደግ**

በውሃማ አካላት የሚደረጉ ማናቸውንም እንቅስቃሴዎች ተገቢ የሆነ ክትትል በማድረግ በውሃማ አካላት አካባቢ የሚደረግን እንቅስቃሴዎች 24/7 ክትትል በማድረግ ብሄራዊ ጥቅምን ማስጠበቅ ያስፈልጋል። ይህንንም ለማድረግ ዘርፈ ብዙ ቅድመ ስራዎች ሊከናወኑ ይችላሉ። ከነዚህም ውስጥ፡-

- የውሃ አውዶች ቁጥጥር ሲስተም መዘርጋት፤

- የጥልቅ ውሃ ቁጥጥር ማድረግ እና የውሃማ አካላት የካርታ ስራ ለወደፊት ግዳጆች በሚሆን መልኩ ማዘጋጀት፤

- በውሃማ አካላት አካባቢ የሚገኙ የመሬት ክፍሎችን ከሌሎች ሃይሎች ጋር በቅንጅት ለመቆጣጠር የሚችል የመረጃ ልውውጥና የስራ ግንኙነት መፍጠር ናቸው።

**ሁሉን አቀፍ የእዝና ቁጥጥር ማበጀት**

አንድን ግዳጅ በተገቢው መንገድ በማከናወን ብሄራዊ ጥቅምን ማስጠበቅ፣ ፀጥታን በማስከበር ሰለምን ለማረጋገጥ እና የሃገርና የህዝብ ሃብቶችን ለመጠበቅ ጥብቅ የሆነ የእዝና ቁጥጥር ስርዐት በእጅጉ አስፈላጊ ነው። በዚህም መሰረት፡-

- የኤሌክትሮማግኔቲክ እና የሳይበር መከላከል አቅምን ማበልፀግ፤

- አውቶሜትድ የሆኑ የመመልከቻ የተኩስ አቅሞችን ማበልፀግ፤

- ዘመናዊና ከፍተኛ ምስጢራዊነት ያለው የኮሚዩኒኬሽን ሲስተም እና የእዝና ቁጥጥር ማዕከል መገንባት፤

**የውሃ ላይ ብሄራዊ ጥቅምን ለማስጠበቅ የሚያግዝ ፖሊስ እና ስትራቴጂ መቅረፅ**

ኢትዮጲያ ከምትገኝበት ቀጠና መነሻ በማድረግ እንዲሁም በአካባቢው ላይ ሃያላን እና ምዕራባውያን ያላቸውን ፍላጎት መነሻ ያደረገ የስነ ልቦና ዝግጅት ማድረግ ተገቢ ነው።

- ብሄራዊ ጥቅምን መነሻ ያደረገ፣ ለዛሬ እና ለነገ መልስ የሚሰጥ እንዲሁም የሚያድግ ፖሊሲና ስትራቴጂ መቅረፅ፤
- ቀጣይነት ያለው የውሃ ላይ እና ቀጠናዊ ጂኦፖለቲካዊ ሁኔታዎችን የሚያጠና ሁሉን አቀፍ የሆነ የጥናትና ምርምር ማዕከል ማቋቋም፤

**የህግ ማዕቀፎችን ማበልፀግ**

ውሃ ዓለም አቀፋዊ ጉዳይ በመሆኑ ተገቢ በሆነ የህግ ማእቀፍ ውስጥ ሆኖ ብሄራዊ ጥቅምን ማስከበር ተገቢ ነው፡፡

- ዓለም አቀፍ የውሃ ላይ ህጎች እና ስምምነቶች የእለት ተዕለት ስራ እንዲሆኑ ለማድረግ ሰነዶችን የጋራ ወደ ሆነ ቋንቋ አስተርጉሞ በስራ ላይ ማዋል፤
- ቀጣይነት ያለው የህግ ትምህርት ማዕቀፍ ማዘጋጀት፤

**በእውቀት ላይ የተመሰረተ የውሃ ላይ ዲፕሎማሲ መዘርጋት**

በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ካለው ነባራዊ ሁኔታ በመነሳት ብሄራዊ ጥቅምን ለማስጠበቅ ዲፕሎማሲ የአንበሳውን ድርሻ መውሰድ ይገባዋል፡፡

- ከጎረቤት አገሮች ጋር ሊኖረን በሚገባ የባህር ኃይል የትብብር ማዕቀፍ ላይ በሰፊው መስራት፡፡ የመረጃ ልውውጥ እና የጋራ ግዳጅ የምንወጣበትን ሁኔታ ቅድሚያ መስጠት፤
- በቀጠናው ካሉ ሃያላንና ጋር በተመሳሳይ በጋራ የምንሰራባቸውን እና የመረጃ ልውውጥ የምናደርግባቸውን ሁኔታዎች ማመቻቸት፤
- ጨቅላ ባህር ኃይል ያለን በመሆኑ በአካባቢው ካሉ ጋር ሁሉ አቅማችንን ለማሳደግ እና ልምድ ለመውሰድ ብዙ መስራት የምንችልበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤
- ከተመረጡ ተቋማት ወይንም አገሮች ጋር በአገናኝ ወይንም ላይዘን አማካኝነት 27/7 ህልውናችንን ማረጋገጥ፤
- የባህር ኃይል ኦፕሬሽናል ቤዝ በሚኖርበት ሁኔታ ላይ ከአገራት ጋር ሰፊ የዲፕሎማሲ ስራ መስራት፡፡ ኦፕሬሽናል ቤዝ ገንዘብ ስለተከፈለ ብቻ የሚገኝ ያለመሆኑን ጠንቅቆ በማወቅ ማሰፈፀም ያስፈልጋል፡፡ ቤዝ እንዲኖረን የምንፈልገው አገር ውስጥ እነማን በተለይ ሃያለን አሉ የሚለውን ጥያቄ መመለስ ተገቢ ነው፡፡ ለምሳሌ በጂቡቲ ቤዝ እንዲኖረን ከፈለግን ሜሪካ፣ ፈረንሳይ እና ቻይና ወዘተ …. ያሉት ሃገራት ተፅዕኖ እንደሚያሳርፉ መገንዘብ ተገቢ ይሆናል፡፡

**ዘመኑን የዋጀ ተቋም መገንባት**

ባህር ኃይልን መገንባት ትልቅ ኢንቨስትመንት የሚጠይቅ ስራ ነው፡፡ ሆኖም ግን አገራችን ካለችበት ጂኦፖለቲካዊ ሁኔታ በመነሳት ቅድሚያ ተሰጥቶት ሊሰራ የሚገባ ፕሮጀክት መሆን አለበት፡፡

- አስፈላጊ የሚባሉ መሰረተ ልማቶችን ጠቅላይ መምሪያ፣ የስልጠና ማዕከል፣ የጥናትና ምርምር ማዕከል የመሳሰሉትን መገንባት፤
- የተማረ እና የሰለጠነ የሰው ኃይል ማፍራት፤
- በተቻለ መጠን በቀጠናው ላይ አገራችን ያላትን ጥቅም ለማስከበር በቀይ ባህር፣ በባብኤል መንደብ እና በምዕራብ ህንድ ውቅያኖስ አካባቢ ያለውን ሁኔታ በጥልቀት ለመረዳት በሚያስችል ሁኔታ ኦፕሬሽናል ቤዝ ማቋቋም፤
- በውስጥ ውሃማ አካላት ላይ የሚደረጉ ስምሪቶችን እንደ መልካም አጋጣሚ በመቁጠር ኦፕሬሽናል አቅምን ማሳደግ፡፡

**አገራዊ አቅሞችን አሟጦ መጠቀም**

ባህር ኃይል መገንባት ብዙ አቅም የሚጠይቅ ስራ ነው፡፡ በፋይናንስ ስሌት ብቻ እንኳን ብዙ ወጪ የሚጠይቅ ነው፡፡ ይህም በመሆኑ በአገራችን በርካታ ተቋማት ባህር ኃይልን ለመደገፍ የሚያስችል አቅም ያላቸው በመሆኑ በትብብር ለመስራት አስፈላጊ ግንኙነቶችን ማድረግ ተገቢ ነው፡፡

- ከውሃማ አካላት ጋር ተያያዥ በሆኑ ጉዳዮች እንደ የውሃማ አካላት ጥልቀት፣ የንጥረ ነገር ይዘት፣ ፍጥነት እና መጠን ጋር በተያያዘ እጅግ የዳበረ ልምድ ባለቤት የሆነው እንደ አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ የመሰሉ ተቋማትን አቅም መጠቀም እጅግ ተገቢ ይሆናል፤

- የውሃማ አካላትን የካርታ ንድፍ ለስልጠና እና ለዘመቻ በሚሆን መልኩ ከነጥልቀታቸው በማዘጋጀት በኩል ከአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ባሻገር የስፔስ ሳይንስ እና ጂኦስፓሻል ኢንስቲትዩት ተባባሪ እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል፤
- የውሃማ አካላትን ለመቆጣጠር የሚያገለግሉ ሰርቪላንስ ሲስተም፣ ኦፕሬሽን ማዕከል በማበልፀግ እና አውቶሜትድ የሆነ አርማመንት ሲስተም ወዘተ ለመገንባት የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደርን የዳበረ ልምድ መጠቀም እጅጉን አዋጪ ነው፤
- ትናንሽ ጀልባዎችን በመገንባት ረገድ የካባድ አቪዬሽን ማዕከል የጀልባ ጥገና ክፍል አቅሞች በጥናት ላይ በመመርኮዝ መጠቀም።

እንዲሁም የባህር ትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ እንዲሁም የማሪታይም ባለስልጣንን አቅም በመጠቀም በፍጠነት ባህር ኃይሉን ማሳደግ እና ኦፕሬሽናል በማድረግ የመከላከያን የማድረግ አቅም እንዲያሳድግ ማድረግ ይቻላል።

## ዋቢ መጽሐፍት


Addis Standard. Senior Naval Officer says Ethiopian Navy preparations consider protecting country from threats, Addis Ababa, June 4, 2021

Berg, W and Meeste, J. "Ports & Power: the Securitisation of Port Politics." Clingendael. 2018. https://www.clingendael.org/sites/default/files/2018-05/Ports_and_Powers.pdf, Accessed on 3 January 2023

Brendon, C. (2018). Quartz Africa. An Ethiopia-backed port is changing power dynamics in the Horn of Africa. Available at https://qz.com/africa/

Cafiero, G & Čok, C. (2020). Analysis: Ports in the Horn of Africa risk becoming new flashpoints in Middle East rivalries.

David, S. (2018). The politics of ports in the Horn: War, peace and Red Sea rivalries. Available at https://africanarguments.org

Davies, C. S. L. "The Administration of the Royal Navy under Henry VIII: The Origins of the Navy Board." The English Historical Review 80, no. 315, 1965: 268–88.

Dawit Fantu (2020), the Military Bases of Saudi Arabia and United Arab Emirates in the Horn of Africa and Implications for Ethiopia Foreign Policy

Dickens Olewe, 14, June 2018, Story why landlocked Ethiopia wants to launch a navy, published in June 2018

Esrael Yohannes 2018, The Expansion of Military Bases in the Horn of Africa: Analysis of Its Challenges and Opportunities to Ethiopia's Policy in the Region, Addis Ababa University

Horton, M. (2019). Hot Issue – The Race for Bases, Ports, and Resources in the Horn of Africa Heats Up. Available at https://jamestown.org

Horton, M. Hot Issue - The Race for Bases, Ports, and Resources in the Horn of Africa Heats Up – Jamestown Foundatin. 11 October 2019. https://jamestown.org/program/hot-issue-the-race-for-bases-ports-and-resources-in-the-horn-of-africa-heats-up/, Accessed on 3 January 2023
Horton, M. Hot Issue - The Race for Bases, Ports, and Resources in the Horn of Africa Heats Up – Jamestown Foundatin. 11 October 2019. https://jamestown.org/program/hot-issue-the-race-for-bases-ports-and-resources-in-the-horn-of-africa-heats-up/, Accessed on 3 January 2023
Mangistu Ejeta (2020), United States and Chinese Military Bases in the Horn of Africa: Opportunities and Risks for Ethiopia, Addis Ababa University

Melvin, Neil. The Foreign Military Presence in the Horn of Africa Region. SIPRI. 2019. https://www.sipri.org/sites/default/files/2019-05/sipribp1904_1.pdf
Melvin, Neil. The Foreign Military Presence in the Horn of Africa Region. SIPRI. 2019. https://www.sipri.org/sites/default/files/2019-05/sipribp1904_1.pdf
Melvin, Neil. The Foreign Military Presence in the Horn of Africa Region. SIPRI. 2019. https://www.sipri.org/sites/default/files/2019-05/sipribp1904_1.pdf
Questions over foreign military presence in Africa - ISS Africa. https://issafrica.org/pscreport/psc-insights/questions-over-foreign-military-presence-in-africa

Reuters, 2018, Landlocked Ethiopia plans new navy as part of military reforms By Aaron Maasho ADDIS ABABA (Reuters) Editing by Jane Merriman

Tesfaye Gebremariam. (2021), Foreign Military Bases in the Horn of Africa and their Implications To Ethiopia's National Security (2002-2019), Addis Ababa University

United Nations Convention on the Law of the Sea. https://www.un.org/depts/los/convention_agreements/texts/unclos/part2.htm

United Nations. "United Nations Convention on the Law of the Sea." https://www.un.org/depts/los/convention_agreements/texts/unclos/part2.htm , Accessed on 3 January 2023.

Urgessa Deressa. (2014), the Ethio - Djibouti Relations: Implications for Sub-Regional Integration Schemes in the Horn of Africa, Addis Ababa University

US Foreign Affairs megazin, 2019

USIP (2020), The Final Report and Recommendations of the Senior Study Group on Peace and Security in the Red Sea Arena considers the, © 2020 by the United States Institute of Peace, First published October

Yohannes, Esrael. “The Expansion of Military Bases in the Horn of Africa: Analysis of Its Challenges and Opportunities to Ethiopia’s Policy in the Region.” Thesis Submitted in Partial Fulfilmentof the Requirements for the Degree of Masters of Art in International Relations and Diplomacy. Addis Ababa University, 2018.

ኃያላን የሚፎካከሩበት የአፍሪካ ቀንድ አገራት ትብብር የት ድረስ ይዘልቃል? - BBC News አማርኛ፤ https://www.bbc.com/amharic/articles/c3grnywjneko

በኢትዮጵያ ከውስጥ እና ከውጪ የሚቃጡ ጥቃቶችን የሚመክት ባህር ኃይል እየተገነባ ነው - የባህር ኃይል ዋና አዛዥ - Fana Broadcasting Corporate S.C. https://www.fanabc.com/archives/120764

አዲሱ የቀይ ባህር ጂኦ ፖለቲከስ እና የሓያላን ሐገራት ፉክክር – ክፍል 1 – Awash FM፤ https://awashfm.com/%E1%8A%A0%E1%8B%B2%E1%88%B1

ኢትዮጲያ፡ ያለ ባሕር በር የባሕር ኃይል? -BBC News አማርኛ፤ https://www.bbc.com/amharic/44409395

ኢትዮጵያ የባህር ሀይል ሰራዊቷን ልታዋቅር ነው - ኢዜአ አማርኛ፤ https://www.ena.et/web/amh/w/am_17199

የባህር በር ከሌለ ባህር ሀይል ማቋቋም ቀልድ ነው፡፡ DW 29.11.2018፤ https://www.dw.com/am/የባህር-በር-ከሌለ-ባህር-ሀይል-ማቋቋም-ቀልድ-ነው/a-46494464